**"ሉአላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ"**
ደራሲ ገብሩ አስራት

አስተያየት
ተስፋይ አፅብሃ

ገብሩ አስራት "ሉአላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" በሚል ርእስ በፃፈው መፅሓፍ በህወሓት አመራር ያልተለመደና የማይፈለግ ግልፅነት በማካተቱ በህወሓት ታሪክ ላይ ሚዛናዊ ግንዛቤ ለማግኘት ይጠቅማል፡፡ ህወሓት ደግሞ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ህይወት ከፍተኛ ትርጉም አለው፡ ስለዚህ ገብሩ ታሪካዊ ሰነድ ለማዘጋጀት ላደረገው ጥረት፣ ትህትና ላለው አፃፃፉና በግልፅነቱ ምክንያት ሊደርስበት የሚችል ችግር ለመቀበል በመቁረጡ ሊመሰገን ይገባዋል፡፡

ገብሩ በኢትዮጵያ የሉአላዊነት ጥያቄ የማያሻማ አቋም ከማብራራቱም በላይ በህወሓት ውስጥ ስለዚህም በኢትዮጵያ ደረጃ ቁልፍ የስልጣን ቦታ የያዙ ሰዎች ከሻዕብያ ጋር በተደረገው የመከላከል ጦርነት ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት ምን ያህል አደገኞች እንደነበሩ በዝርዝር አቅርቧል፡፡

ሁለቱ የመፅሃፉ ርእስ አካል የሆኑት "ሉአላዊነትና ዴሞክራሲ" ለየብቻቸው ቢገለፁም ትስስር አላቸው፡፡ ገብሩ የዴሞክራሲ አለመኖር ሉአላዊነትን እንደጎዳ ቃል በቃል ባይገልፀውም በዝርዝር ያቀረባቸው ጭብጦች ይህን ትስስር ያስገነዝባሉ፡፡ ከፊሉ የህወሓት አመራር ለተሚላ ያገራችን ሉአላዊነት አለመቆሙ ብቻ ሳይሆን ፀረ ዴሞክራሲነቱን ማለትም አምባገነንነቱን ለሉአላዊነት በፅናት የቆሙትን ለማባረርና ለመቅጣት፣ በጥቅም የሚደለሉትን ደግሞ እንዲደግፉት ለማድረግ ተጠቅሞበታል፡፡ ስለዚህ አፈናው ሉአላዊነትን ለመሸራረፍም መሳሪያ ተደርጓል፡፡

ገብሩ ስለ ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች መረገጥ የፃፈው ለኢትዮጵያውያን አዲስ ነገር ባይሆንም የገዢው ፓርቲ ባለ ስልጣኖች አፈናው ከትጥቅ ትግሉ ጀምረው የለመዱት መሆኑን ማስረጃ በማቅረቡ፣ ከነሱ ለውጥ መጠበቅ ትርጉም እንደሌለው ያስገነዝባል፡፡

ገብሩ የጠቀሰው በትጥቅ ትግሉ ጊዜ ሲካሄድ የነበረው "ምርጫ" አሁን ኢህአዴግ ከሚያካሂደው "ምርጫ 99% +" ጋር ምን ያህል እንደሚመሳሰል ለመገንዘብ በተለይ የ"ምርጫ" አዘጋጅ ኮሚቴውን (የወቅቱ ምርጫ ቦርዱን) ሁኔታ ማብራራት ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡ በወታደራዊው ሸንጎ ከተመረጡት 10 የአዘጋጅ ኮሚቴ አባሎች አብዛኞቹ (6ቱ፡ሰዓረ፣ ገብሩ፣ ተሾመ፣ ፃድቃን፣ መስፍንና፣ አባዲ/ጎሊያድ ወልደገብርኤል (ገብሩ በመፅሃፉ 'አባዲ ታፈረ' የሚለው) የአባሎች መብቶች እንዲከበሩ የሚፈልጉ እንደነበሩ አስቀድሞ ይታወቅ ነበር፡፡

ገብሩ በገፅ 87 ላይ ያስር ያዘጋጅ ኮሚቴ አባሎች የስም ዝርዝር ሰጥቶ በገፅ 97 ላይ የሰባቱን ብቻ ፎቶግራፎች ለጥፈዋል፡፡ ሶስቱ ለምን እንደጎደሉ ገብሩ አልጠቀሰም፤ የጎደሉት አባዲ ጎሊያድ ስለተገደለ (ራሱን እንደገደለም የሚገልፁ አሉ፤ በህወሓት ውስጥ ግልፅነት ስለሌለ መሞቱም አሟሟቱም በይፋ አልተገለፀም)፣ መስፍን አማረ ስለታሰረና ተሾመ ጉዶ ከድርጅቱ አምልጦ ስለወጣ ነው፡፡ በወታደራዊው ሸንጎ ስብሰባ ላይ አዘጋጅ ከሚቴው የማእከላዊ ኮሚቴው መሳሪያ እንደሚሆን የነበረ ስጋት በግልፅ ቀርቦ ነበር፤ ምክንያቱም ብዙ አባሎች በስልጣን ላይ የነበሩት ሰዎች በቅንነት ይሰራሉ የሚል እምነት አልነበራቸውም፡፡ ተወልደ ወልደማርያም ሁሉንም በጥርጣሬ መንፈስ 'የተቆጣጣሪውን ተቆጣጣሪ' እያልን ከቀጠልን ማቆሚያ ስለማናገኝለት እንደ ጓዶች መተማመንም እንዲኖረን አጥብቆ ስለተማፀነ ስብሰባው ተጠቃልሎ ተዘጋ፡፡

ገብሩ፡ "የታጋዩን መብት በማስከበር ድርጅቱን ወደ ተሻለ የዴሞክራሲ እድገትና ጥራት እንድናሻግር በወታደራዊ ሸንጎው የተመረጥነው የአዘጋጅ ኮሚቴ አባላትም በአመራሩ ተሸንፈን የአመራሩን ፍላጎትና መፈክር አራማጅ ሆንን" (ገፅ 88) ብሏል፡፡ ከዚህ በላይ እንደጠቀስኩት ግን በወታደራዊው ሸንጎ ስብሰባ ስለነበርኩ የታጋዩ መብት እንደማይከበር አስቀድሞ ታወቆና ተደጋግሞ ተገልፆ ነበር፡፡ በተሓህት/ህወሓት ውስጥ ስልጣኑን ቀድመው የተቆጣጠሩት ጥቂት ሰዎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች እየወሰዱ አፈናቸው እንጂ አብዮታዊ መንፈስ ይዘው የተሰለፉ፣ እኩልነትና ፍትህ እንዲሰፍን የሚፈልጉ ሆኖም ለውጥ ማምጣት ያልቻሉና በህይወታቸው የከፈሉ ወጣቶች እንደነበሩ መጥቀሱ ተገቢ ነው፡፡

ህወሓት ወታደሮች እንዲማረኩለት ለመስበክ የምርኮኞችን መብት እንደሚያከብር ብዙ ይቀሰቅስ ነበር፡፡ በራሳቸው ሃሳብ የሚመሩና እንደ መሳሪያ ሆነው የማያገለግሉትን፣ ምናልባትም በተቃዋሚነት ህዝብ ሊያሰባስቡ የሚችሉትን ምርኮኞች እንደሚረሽን ግን ገብሩ ካጋለጠው የኢህአፓ አባሎች መረሸን መረዳት ይቻላል፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ተወዳዳሪ የሌለው በህዝብ ላይ ጭፍጨፋ ያካሄዱ የደርግ ባለስልጣኖች፣ ጠበቆች ቆመውላቸው፣ ክሳቸው ለአለም አቀፍ ታዛቢዎች ክፍት ሆኖ ከቆየ በሁዋላ በምህረት ሲለቀቁ፣ ከኢህአፓ የተማረኩት በድብቅ መገደላቸው የጦርና የኢሰብአዊነት ወንጀል ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡

ገብሩ ባቀረባቸው ሃሳቦች ላይ መሠረታዊ ልዩነት የለኝም፡፡ በዝርዝር ላይ ግን የመፅሓፉ ይዘት ሰፊ ስለሆነ ከዛ በላይ መጨመር ነበረበት ባልልም፣ አጠቃላይ የመፅሓፉ ግምገማ ሳይሆን ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባ ነበር የምላቸውንና ስለነበርኩባቸው (በተወሰኑ ድርጊቶች ዝርዝር ለሚፈልጉም) የማውቃቸውን ጥቂት ነጥቦች መጥቀስ እፈልጋለሁ፡፡ እነሱም፡

1. ለአንድነት ያልቆሙ ለሉአላዊነት አለመቆመቸው
2. የግፍ ግድያዎች፣ የፈጠራ ቀውሶችና ኢዴህ
3. ተሓህትና ኢህአሠ ሶበያ ላይ ለምን እንደተዋጉ

በሚሉ ርእሶች ተጠቃልለዋል፡፡

### 1. ለአንድነት ያልቆሙ ለሉአላዊነት አለመቆመቸው

ገብሩ መፅሃፉ ከተሰራጨ በሁዋላ የተለያዩ ሰዎች በግለ ሰቦች ላይ እንዳተኮረ ሂሳዊ አስተያየቶች ሲያቀርቡበት ትኩረቱ በተቋሞች ላይ እንጂ በግለ ሰቦች ላይ እንዳልሆነ ይገልፃል፡፡ ደራሲው ሰዎችን የጠቀሰው ሃሳባቸውንና ድርጊታቸውን እያቀረበ እንጂ ሰዎችን ነጥሎ አይደለም፤ ብዙ ቅፅሎች እንዳይጠቀም መጠንቀቁም ከአፃፃፉ ጎልቶ ይታያል፡፡ ተገቢ የማይሆነው ካለ በቂ ምክንያትና ማስረጃ የግለ ሰቦች ስም በመጥፎ ቢያነሳ ኖሮ ነበር፡፡

ሃሳቦች፣ ድርጊቶችና ተቋሞች ሰዎች በሌሉበት በተአምር አይከሰቱም፡፡ ለጥሩም ይሁን ለመጥፎ የተወሰኑ ሃሳቦች ያፈለቁ ወይም የተለያዩ ሃሳቦች አጠራቅመው ያቀነባበሩ ሰዎች በእነዛ ሃሳቦች መሰረት ድርጊቶች ሲፈፅሙ፤ እንደዚሁም ሃሳቦቻቸውና ድርጊቶቻቸው ቀጣይነት እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ተቋሞች ሲመሰርቱ ከተሳካላቸው ዞሮ ዞሮ ገገር የሚሆነው የጀማሪዎቹ ፍላጎት ነው፡፡ ስለዚህ እንደ ምሳሌ ከወስድን በጀርመንና በጣልያን ካለ ሂትለርና ሙሶሎኒ ስለ ናዚና ፋሽስት ተቋሞች መፃፍ በቂ አይደለም፡፡ ግለ--ሰቦች አመቺ ሆኖ ባገኙት የታሪክ አጋጣሚ ምን ያህል ጥፋት ወይም እድገት ሊያስከተሉ እንደሚችሉ ለመገንዘብ የሰዎቹ ማንነትም መግለፅ ያስፈልጋል፡፡ ይኸም ግንዛቤ በተመሳሳይ ሁኔታ ተመሳሳይ ድርጊቶች ሊፈፅሙ የሚችሉ ሰዎችን በወቅቱ ለመግታት ወይም ለመደገፍ ለመዘጋጀት ይጠቅማል፡፡

ከ1990 እስከ 1992 ከሻዕብያ ጋር በተደረገው ጦርነት በቀረበው የአስታራቂዎች ሃሳብ አፈፃፀም ላይ ተወረው በቆዩት የኢትዮጵያ ቦታዎች ከወረራው በፊት የነበሯቸውን መንግስታዊ ተቋሞች ሙሉ ለሙሉ ሳይመለሱላቸው እንዲቆዩ የሚያደርግ ነበር፡፡ በዝርዝር ገብሩ እንዳቀረበው ቴክኒካል ቅንጅቱ፡

- ሀ. ግጭቱን ለማስቆም ከመፈረማችን በፊት የተወረረው መሬታችን ተለይቶ መስማማት አለብን ብለን ባቀረብነው ሃሳብ ላይ ስምምነት ላይ ሳይደረስ ግጭት እናቆማለን ብላችሁ ፈረሙ የሚል ሰነድ ነበር፡፡
- ለ. ሚሊሽያችን ትጥቁን ፈትቶ ጸጥታ የማስከበሩ ተግባር በፖሊስ ስር እንዲሆንም በሰነዱ ሰፍሮ ነበር፡፡ ይህ አቋም.... ከወረራው በፊት ይፈጽም የነበረውን ተግባር እንዳያከናውን የሚከለክል ነው፡፡...
- ሐ. ሰነዱ በጸጥታ ሁኔታ ኤርትራውያንን ወዳገራቸው መላክን ይከለክላል፡፡...
- መ. ሰነዱ ምንም አይነት ማሻሻያ ሊደረግበት እንደማይችል ተሰምሮበት "ተቀብለነዋል ወይም አልተቀበልነውም የሚለውን መልስ ብቻ ነው የምንፈልገው" የሚል መልእክትም ነበረው፡፡ (ገጽ 298)

ይህ ሉአላዊነትን የሚፃረረውን ሃሳብ የብአዴንና ኦሕዴድ የማእከላዊ ኮሚቴ አባሎች በሙሉ ድምፅ. የደኢሕዴግ ደግሞ ከ 51 የማእከላዊ ኮሚቴ አባሎች ከሁለት በስተቀር 49ኙ ማለትም በ96% ሲቃወሙት የህወሓት የማእከላዊ ኮሚቴ አባሎች ግን በመለስ መሪነት ከ43% በላይ ሉአላዊነት

የሚፃረረውን ሃሳብ መቀበላቸው ቢያንስ አስገራሚ ሊባል የሚገባው አቋም ነው፡፡ በትግራይ ስም የሚጠራውና ለትግራይ ህዝብ እንደቆመ የሚገልፀው ህወሓት ከሁሉም በላይ በሻዕብያ የተጨፈጨፈው፣ ታፍኖ የተወሰደውና ከቀየው የተፈናቀለው ሰላማዊ የትግራይ ህዝብ መሆኑን እያወቀ ለምን የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ሳይሸራረፍ እንዲከበርና የትግራይ ህዝብ ከወረራው በፊት የነበሩትን ተቋሞች እንዲመለሱለት የማይቀበሉ ሰዎች በዙበት? የሚል ጥያቄ እንዴት ይመለሳል?

መለስ 'ሰነዱን ካልፈረምን ...እርዳታ አናገኝም፣ ነዳጅ አናገኝም፣ ጉሮሮአችን ይታነቃል' ወዘተ... ብሎ ነበር (ገጽ 302)፡፡ ሰነዱ አልተፈረመም፤ ስላልተፈረመ ግን በኢትዮጵያ ላይ መለስ ያለው ችግር አልደረሰም፡፡ ስዩም 'የጦርነት መንገድ እንምረጥ ብንል ሁለታችንም ከባድ ቁስል ተሸክመን ከመለያየት ያለፈ ለውጥ አይኖረውም' (ገጽ 302) ብሎ ነበር፡፡ ጦርነቱ ቀጥሎ ግን ለውጥ መጣ፤ሻዕብያ የወረራቸውን ቦታዎች ለቀቀ፤ ተፈናቅሎ የነበረው ህዝብ ወደ ቦታው ተመለሰ፡፡ ስብሓት 'ዛላንበሳም ይሁን ዓሊተናን ሻዕብያዎች ለሃያና ለሰላሳ አመታት ቢቆጣጠሩት ደንታ ...የለኝም' (ገጽ 303)፡፡ ብሎ ነበር፡፡ ከዓሊተና/ኢሮብ ታፍነው የተወሰዱት ኢትዮጵያውያን አልተመለሱም እንጂ ዛላንበሳና እና ዓሊተና ከሻዕብያ ቁጥጥር ወጡ፡፡ የስብሓት ደንታቢስነትም ዜጎች ሊጋሩት አይችሉም፡፡

በህወሓት ውስጥ ሉአላዊነትን ለድርድር የሚያቀርቡ ሰዎች መብዛታቸው ሉአላዊነትና ዴሞክራሲ እንደሚያያዙም ያመለክታል፤ ምክንያቱም ዘግይተው የማእከላዊ ኮሚቴ አባሎች የሆኑት ቀድመው ስልጣኑን በተቆጣጠሩት ሰዎች ፍላጎት እንጂ በታጋዩ ወይም በህዝብ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አይደለም፡፡ ስለዚህም ታማኝነታቸው ለህዝብ ሳይሆን ለሾሚቻቸውና ሊያባርሯቸው ለሚችሉ ሰዎች ስለሆነ ከመለስ ጋር መቆማቸው ለግል ጥቅምም ይመስላል፡፡ ትግራይ ውስጥ ስልጣን የነበራቸው ሰዎች የመለስን አቋም ከማወቃቸው በፊት ወረራውን ለመከላከል በነበራቸው ቁርጠኝነት ከነገብሩ አይለዩም ነበር (ገፅ 271/72)፡፡

ገብሩ ለምን እነ መለስ ባገራችን ሉአላዊነት ለመደራደር እንደፈለጉ ሲጠየቅ የሚሰጠው መልስ፣ ስልጣናቸውን እንዳያጡ ስለሰጉ ሊሆን እንደሚችል ጠቅሷል፡፡ በዚህ አገላለፅ የራሱን ስልጣንና ከስልጣን የሚያገኘውን ጥቅም ካገር ሉአላዊነት በላይ የሚያስቀድም ቡድን መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ሰራዊት የበላይነቱ ካረጋገጠ በሁዋላ ቡድኑ ከኤርትራ መንግስት እንዳይመጣበት የፈራው ስጋት ተወግዶም ኢትዮጵያን የመጉዳት ድርጊቱን አልቀየረም፡፡ ከህወሓት በስተቀር ሌሎቹ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ከህወሓት ነፃ የሆኑ ድርጅቶች ባይሆኑም በህወሓት ውስጥ ኢትዮጵያዊ ሃይል እሰከነበረበት ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ ሉአላዊነት ለመደራደር ዝግጁ አልነበሩም፡፡

ይህ አስገራሚ የክህደት አቋም ከሁለት ሌሎች ተመሳሳይ አቋሞች ጋር ትስስር አለው፤ ምክንያትም ሉአላዊነትን የሚጎዱ ሃሳቦች የሚያቀርቡትና የሚፈፅሙት ዋናዎቹ አንድ አይነት ሰዎች ናቸው፡

1. የኢትዮጵያን ሉአላዊነት የሚፃረረውን ቴክኒካል ቅንጅት የተቀበሉት እና ሌሎችንም ከነሱ ጋር ሊያሰልፉ የቻሉት፣ አባይ ፀሃየ ለጊዜው ከነሱ አፈንግጦ ቢቆይም ዋናዎቹ ተዋናያን የኢትዮጵያን አንድነት የሚፃረረውን ትግራይን የመገንጠል ማኒፌስቶ የፃፉት መለስ፣ ስብሓትና ስዩም ናቸው፡፡(ካሕሳይ በርሀ፡ 70[1]፣ አረጋዊ በርሀ፡ 196[2]) ገብሩ ማኒፌስቶውን በሚመለከት፡ "ውሳኔው ሲወሰን፣ ረቂቁ ተፅፎ ሲላክና ሲሰራጭ አልነበርንም የሚሉት የአመራር አባላትም ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት ካልሆነ በስተቀር ያን ያህል (እ)ንዝህላል ነበሩ ማለት የዳግታል፡፡" ብሎ ሰባቱ የአመራር አባላትና መለስ ዜናዊ በዚህ ጉዳይ ሃላፊነት መውሰድ እንዳለባቸው ይጠቅሳል(ገፅ 98)፡፡ ገብሩ እንደሚለውም ቢሆን አራቱ ከሻዕብያ ጋር ውግያ ሲደረግ አልነበሩም (ሁለቱ፣ ሙሴ ተክሌና ዘርኡ ገሰሰ በህይወት አልነበሩም፤ ሁለቱ፣ አረጋዊ በርሀና ግደይ ዘርአፅዮን ደግሞ በህወሓት ውስጥ አልነበሩም፡፡)
2. ኢትዮጵያን እንደ ቅኝ ገዢ ኤርትራን እንደ ቅኝ ግዛት የፈረጁም ማኒፌስቶውን የፃፉት ሰዎች ናቸው፡፡

ገብሩ፣ ተሓህት ኤርትራን እንደ ቅኝ ግዛት ማየቱ በጥናት ላይ የተመሰረተ እንዳልነበረ (ገፅ 99) መግለጹ ትክክል ነው፡፡ ለዚህ ስህተት የጋራ ሃላፊነት ለመውሰድ የሚያደርገው ሙከራ በሚመለከት ግን ከድርጅቱ አሰራር አንፃር ተያይዘው መነሳት ያለባቸው ጥያቄዎች አሉ፡

---

1 Kahsay Berhe,: Ethiopia: Democratization und Unity, ቭረላገሰሃዩሰ ሞነስነሰትነ ዩነደ ቫንረዳት 2005

2 Aregawi Berhe: A Political History of the Tigray People's Liberation Front (1975 – 1991), Amsterdam 2008

1ኛው ጥያቄ ማኒፌስቶውን የጻፉት ሰዎች ኤርትራን በሚመለከት በጥናት ላይ የተመሰረተ አቋም እንዳልወሰዱ ያምናሉ ወይ? የሚለው ነው፡፡ መለስ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርገው አቋሙ በጥናት ላይ የተመሰረተ ለማስመሰል የኤርትራ ቅኝ ግዛትነት በታሪክ፣ በህግና በፖለቲካ ኢኮኖሚ የተረጋገጠ መሆኑን ፅፏል (ለንፅፅር፡ የኤርትራ ህዝብ ትግል ከየት ወዴት! [ግምገማ} ህ.ወ.ሓ.ት፣ 1979)፡፡

2ኛው ጥያቄ በተሓህት/ህወሓት/ማሌሊት ውስጥ ኤርትራ ቅኝ ግዛት መባልዋን መቃወም ይቻል ነበር ወይ? የሚለው ነው፡፡

ለዚህም መልሱ፣ ማኒፌስቶውን የፃፉት ሰዎች ተሓህትን/ህወሓትን እንደተቆጣጠሩ፣ ከ70ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ደግሞ መለስ ፍፁም ስልጣን ስለያዘ (መለስ ማሌሊትን ለመመስረት ባደረገው ዝግጅት በ1975 መሪ ህዋስ (መሪሕ ባእታ) አቋቋሞ፣ በ1977 ማሌሊትን መስርቶ ነበር፡፡) ድርጅቱ ዴሞክራሲያዊ እንዳልነበረና እንዳልሆነ፣ የኤርትራ ቅኝ ግዛት መባል በሚመለከት በጥቂት ሰዎች በማኒፌስቶው ከተፃፈ በሁዋላ በተሓህት/ህወሓት ውስጥ እንደ አጀንዳ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት እንደማያውቅ፣ የተለየ ሃሳብ የሚያቀርቡ ሰዎች እንደሚፈረጁና ክትትል እንደሚደረግባቸው፣ አዲስ ሃሳብ በሚመለከት በፅሑፍ ፈቃድ ከመጠየቅ በፊት መነጋገር እንደማይፈቀድ[3] ያደባባይ ምስጢር ነው፡፡

ስለዚህ ገብሩ 'እኛ' ብሎ የኤርትራ ጉዳይ ስላልተጠና ተሓህት የተሳሳተ አቋም ወሰደ ቢል ምክንያታዊ አይሆንም፡፡ 'እኛ' በሚለው ተራውን አባል ካካተተ መብት የሌለው አባል በድርጅት አቋም ላይ መወሰን ስለማይችል አይሰራም፡፡ 'እኛ' በሚለው የማኒፌስቶው ጸሓፊዎቹን ካካተተ የእነሱ ፍላጎት ኤርትራን ማስገንጠል እንጂ የጥናት ጥያቄ ስላልነበረ ከማይፈልጉት ሰዎች ጋር ይሰለፋል፡፡ 'እኔ' ተሳስቼ ነበር ቢልም፣ ባይሳሳትም ኖሮ ድርጅቱን ጥሎ መውጣት ይችል ነበር፤ ካልተባለ በስተቀር ድርጅቱን ከተቆጣጠሩት ሰዎች የተለየ ሃሳብ አቅርቦ ለውጥ ሊያመጣ አይችልም ነበር፡፡

ስለዚህ ገብሩ፣ እንኳንና በኤርትራ ጥያቄ ከኤርትራ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ጉዳይ በነበረው ልዩነትም ከማኒፌስቶው ፀሓፊዎች ስልጣኑን የጠቀለለው መለስ ከድርጅቱ እንዳባረረው እየታወቀ የመለስን አቋም በመጋራት ሃላፊነት ለመሸከም መሞከሩ ግልፅ አይደለም፡፡ ገብሩ በወቅቱ ተገንዝቦት ሊያርመው ቢሞክርም ኖሮ የማይችለውን ስህተት መጋራቱ ስርአቱን በጭፍን ከሚደግፉና ክርክራቸው 'አንተም ነበርክበት' ከሚሉት ሰዎች ጋር ለመነጋገር ይጠቅመዋል፤ 'አዎ'፡፡ብሎ ከዚጋ ክርክሩ በእሱ ላይ መሆኑ ቀርቶ በይዘቱ ላይ የመሆን እድል አለው፡፡

ስህተትን በመጋራት ሃላፊነትን መውሰድ በሚመለከት የገብሩ አቀራረብ ከመፅሃፉ ጋር የተያያዘ ውይይት በይዘት ላይ እንዲያተኩር የሚረዳ ቢሆንም አንድ በዚህ የማይፈታ መሰረታዊ ችግር አለ፡፡ ይህ ችግር የመብት አልባ ባለስልጣኖች የአጣብቂኝ ችግር ሊባል ይችላል፡፡ የቀኝም (ለምሳሌ ሂትለር) ይሁን የግራ (ለምሳሌ ስታሊን) ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን ባለበት አገዛዝ የተወሰነ፣ ትልቅም የሆነ ስልጣን ያላቸው ሰዎች አምባገነኑን የመቃወም መብት የላቸውም፡፡
እንደዚህ አይነት ባለስልጣኖች ስህተት ሲፈፀም በወቅቱ እንዳይቃወሙ አምባገነኑ እንደሚያጠቃቸው ስለሚያውቁ መቃወም አይችሉም፡፡ በልዩነታቸው ምክንያት አገዛዙን ጥለው ከማይወጡት መካከል መውጣት ያልቻሉ፣ ጥቅም እንዳይቀርባቸው መውጣት ያልፈለጉ ወይም የሚቃወሙት ብቻ ሳይሆን የሚደግፉትም አቋም ስለነበራቸው ቅሬታ እያላቸው መቆየትን የመረጡ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ከነዚህ ሰዎች ውስጥ ስህተት እንደሰሩ በሚጠየቁበት ጊዜ ስህተቱ እንደማይመለከታቸው እንዳይገልፁ የራሳቸው አቋም ያልነበራቸው ተነታኞች መስለው እንዳይታዩ የሚያስፈራቸው ክብረ-ነክ ጉዳይ ይሆንባቸዋል፡፡ ስለዚህ ስህተቱን ክደው በመከራከር ማሳመን የማይችሉ ከሆነ ለስህተቱ ሃላፊነት

3 በተሓህት/ህወሓት ስም በፅሑፍ የሌለ በአሰራር ግን የተለመደ ካለ ፈቃድ አቋም ነክ አጀንዳ አለማንሳት ነው፡፡ በማሌሊት መሰረታዊ ህግ ግዴታውን እንደ መብት በተሸፈለነ መልክ ገፅ 9 ሐ "አዲስ ሃሳብ እንዲሰራጭለት የሚፈልግ አባል ሃሳቡ ወደ ማእከላዊ ኮሚቴ ልኮ አስፈቅዶ ሃሳቡ እንዲዘረጋለት ማድረግ ይችላል እያለ ይቀጥላል፡፡ (ለንፅፅር ናይ ማርክሰ-ሌኒናዊ ሊግ ትግራይ መሰረታዊ- ሕጊ [ህንፃ] ሓምለ 1977 ዓ.ም ማንበብ ይቻላል)፡፡ በህወሓት ውስጥ ካለ ምንም ተቃውሞ የተለመደው ታጋዮች አመራሩ ባልፈቀደላቸው አጀንዳ እንዳይወያዩ የተደረገው እገዳ በሕዴን የጦፈ ክርክር አስነስቶ፣ ታምራት ላይኔ የላብ አደር ርእየተ አለም እንዳይበረዝ እገዳውን ሲደግፍ ያሬድ ጥበቡ ታጋዮች በፈለጉት ርእስ እንዲወያዩ ተከረከሮ ነበር፡፡ በህወሓት ጣልቃ ገብነት እገዳው እንደፀና ተደረገ፡፡

ይወስዳሉ፡፡ ምናልባት ስህተቱ በወቅቱ ስላልታያቸውም ሊሆን ይችላል፤ ከአቅማቸው አንፃር ስህተቱን ማየት ሊያቅታቸው እንደማይቸል ግልፅ ከሆነ ግን ለትእዝብት ያጋልጣቸዋል፡፡ ከዚህ ሁሉ አጣብቂኝ የሚያወጣው መፍትሄ እውነት ስለሆነ፤ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን መኖሩን ማመን ነው፡፡

ባገራችን ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ ህወሓት በመለስ ቁጥጥር ስር ወድቆ ነበር፡፡ ይህ ላንድ ሰው የመገዛት እውነታ ከግለ-ሰቦች አልፎ ህወሓት ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ብቁ አለመሆኑንና አጠቃላይ የህብረተ-ሰባዊ ሁዋላ ቀርነት መገለጫ ነው፡፡ እነ ገብሩ ጦርነቱ የሚያስከትለውን አደጋ ስላዩ መለስን ለመቃወም ተገዷል፤ ከዛ በፊት መቃወም የሚችሉ የነበሩ አይመስለኝም፤ ከተቃወሙም በሁዋላ ምን እንደደረሰባቸው አይተናል፡፡ የህወሓት ባለስልጣኖች ወደ ቅራኔ ለመግባት ከመገደዳቸው በፊት የመቃወም ነፃነት ቢኖራቸው ኖሮ ኢትዮጵያ የአሰብ የባህር በር[4] እንደሚገባትና እጅግ የሚያስፈልጋት እንደሆነ ለመገንዘብ የሻዕብያ ወረራ አያስፈልጋቸውም ነበር፡፡

ከወረራው በሁዋላም መለስ የባህር በርን ከፀጉር አስተካካይ አገልግሎት ጋር ሲያመሳስል፣ ገብሩ የባህር በር ለአገር ደህንነትና ኢኮኖሚ ያለውን አስፈላጊነት ገልጿል፡፡ ማን ትክክለኛ አቋም እንደገለፀ ለህሊና ፍርድ መተውና ህወሓት የማን አቋም እንደሚያራምድ ማየት ይቻላል፡፡ እንደዛም ሆኖ ያሸነፈው መለስ ነው፡፡ አሸናፊነት በሚመለከትም በኢትዮጵያውያን ውሰጥ በጣም የተዛባ ግንዛቤ ያላቸው ማሸነፍን ከዓላማ ነጥለው የሚያዩ ሰዎች አሉ፡፡ ቢያንስ የአድዋ ድል የምናከብረው ከነፃነት ጋር የተያያዘ ስለሆነ እንጂ በጉልበት ወይም በጥበብ ኢትዮጵያውያን ስላሸነፉ ብቻ አይደለም፡፡ ለህዝብና ላገር መብትና ጥቅም ታግለው የተሸነፉ ዞሮ ዞሮ አለማቸው ያሸንፋል፡፡

ማርክስነትና ወጣትነትም በተሓህት ለተወሰደው አቋም ወሳኝነት እንዳልነበረቸው ኢህአፓና መኢሶን የተለየ አቋም በመውሰድ መልሰውታል፤ እነሱም ማርክሲስቶችና ወጣቶች ነበሯቸው፡፡ ስለዚህ የማኒፌስቶው ፀሓፊዎች ለምን ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል ፈለጉ? ለሚለው ጥያቄ በኢትዮጵያ ደረጃ ስልጣን ሊይዙ እንደሚችሉ ባላወቁበት ጊዜ ትግራይንም ለመገንጠል ስለፈለጉ፤ ኢትዮጵያን መግዛት በቻሉበት ጊዜ ደግሞ ሻዕብያ ስልጣንና ጥቅም እንዳይጋራቸው የወሰዱት አቋም ይመስላል፡፡

ገብሩ የኤርትራ ህዝብ ነፃነቱን ስለፈለገ ሰብአዊ እልቂቱ ከሚቀጥል ነፃነቱን መቀበሉ ተገቢ መሆኑን መግለፁ የሚያከራክር አይደለም (ገፅ 477)፡፡ በአጠቃላይ ከተሓህት ማኒፌስቶ ፀሓፊዎችና ጥቂት ደጋፊዎቻቸው በስተቀር በህወሓት አባላት ውስጥ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያውያን ጋር አብረው መኖር አይችሉም የሚል እምነት አይንፀባረቅም ነበር፡፡ባንፃሩም በህወሓት ውስጥ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያውያን ጋር ለመኖር በጉልበት እንዲገደዱ ፍላጎት እንደነበረ የሚያሳይ ምልክት አልነበረም፡፡

በአንድ በኩል በንጉሱና በደርግ አገዛዞች በኤርትራ ህዝብ ላይ በደሎች ስለተፈፀሙ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የኤርትራ ድርጅቶች ህዝቡ አገዛዙን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን እንዲጠላ ስለቀሰቀሱትና በጉልበት ስላሸማቀቁት ሊሆን አልቻለም እንጂ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ጨቋኞቻቸውን ለማስወገድ ተጋግዘው በእኩልነት ላይ በተመሰረተ አንድነት አብረው መኖር የማይችሉበት ምክንያት አልነበረም፡፡ እንዲያውም የተሻለ እድገትና ጥንካሬ ይኖራቸው ነበር፤ በመለያየታቸውም ሁለቱም ተጎድተዋል፡፡

የተሓህት ማኒፌስቶ ፀሃፊዎች ግን ያንድነት ወይም የሰላማዊ መፍትሄ አማራጭ የሚያነሱትን ኤርትራውያንን ሳይቀር ያብጠለጥሉ ነበር፡፡ ለምሳሌ "የኤርትራ የጠመንጃ አፈሙዝ ወደ ታች አይዘቀዘቅም" በሚል ርእስ 'እኛ' እያለ መለስ የፃፈው መፅሓፍ ኤርትራዊውን ተስፋፅዮን መድሃንየን (ፕሮፌሰር) በመስደብ[5] የተመላ ሲሆን መለስ ተስፋጽዮንን እንደ መንደርደሪያ ተጠቀመበት እንጂ

---

4 በ 1983 ኢህአዴግ፣ አነግና ሌሎች ባደረጉት ስብሰባ (ኮነፈረንስ) ተወልደ ወልደማርያም የባህር በር ጥያቄ አንስቶ እንደነበረና ሊቀ መንበሩ ስለዘጋው ውይይት እንዳልተደረገ ዶክተር በየነ ጴጥሮስ ለደጀን ረደዮ ገልፀው ነበር፡፡

5 በለንደን የህወሓት ፅ/ቤት የፅሑፉን ይዘት ሳይሆን ቃላቱን ለማረም ሞክረን በአንድ ገፅ ብቻ 16 ጊዜ ውሸታምና የዋሸ የግስ እርባታ የሚመስል ሲዋሽ፣ ዋሽቶ.ወዘተ አግኝተን ወደ ሱዳን በቴሌፋክስ ልከን ነበር፡፡ አንዳንድ ሰዎቸ መለስ ሲሳደብ ሰምተው ስድብ የበረሃ ልምድ ይመስላቸዋል፡፡ ሜዳ ላይ በህወሓት ውስጥ እያንዳንዱ አባል ስድብ፣ ዛቻ፣ ቁጣ፣ ፉከራ መጣላት፣ ማሸሚጠጥ ለመተው ላንድ ሳምንትም አይቆይም ነበር፡፡

ፍርሃቱ ሻዕቢያ የተስፋፅዮን አይነት አቋም እንዳይወስድ፣ ከወሰደ ደግሞ በተስፋጽዮን ላይ የወረደው ስድብ ለሻዕቢያም[6] ሆኖ የህዝብ ድጋፍ እንዲያጣ ነበር፡፡ መለስ በ1980 በለንደን የህወሓት ፅ/ቤት ሻዕቢያ ዐሰብን ትቶ የቀረውን በመገንጠል ወይም በፌደሬሽን ከደርግ ጋር እንዳይታረቅ ስጋቱን ይገልፅ ነበር፡፡

በህወሓት ውስጥ የህወሓት አመራር በጥርናፌ (ማእከላዊነት/አፈና) ሌሎች አማራጮችን ዘግቶ ኤርትራን ለማስገንጠል የሚያደርገውን ቅስቀሳ የመቃወም መብት አልነበረም፡፡ ህወሓት ኤርትራውያን ከኢትዮጵያውያን ጋር አብረው መኖርን እንዲመርጡ ቢቀሰቅስም ኖሮ ሻዕቢያ በተቆጣጠረው የኤርትራ ህዝብ ውሳኔ ላይ ለውጥ ሊያመጣ ባይችልም ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ኤርትራውን የተወሰነ ነፃነት አግኝተው የፈለጉትን መምረጥ ይችሉ ነበር፡፡ መለስ ግን ኤርትራ ሳትገነጠል እንዳትቀር የሚያሰጋው ሁኔታ ሳይኖር እንደ ኢትዮጵያውያን በመኖር ላይ የነበሩትን ኤርትራውያን በሻዕቢያ ቁጥጥር ስር እንዲወድቁና መገንጠልን እንዲመርጡ በኢህአዴግም ጫና እንዲደረግባቸው አድርጓል፡፡

በውጭ የህወሓት ደጋፊዎች ማእከላዊነቱ እንደ አገር ቤት ስለማይጠብቅባቸው ኤርትራን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ማንሳት ይችሉ ነበር፡፡ ለምሳሌ በ1987 (1979) ከሎን ውስጥ በተደረገው የህወሓት የብዙሃን ማህበር ስብሰባ የኤርትራ ህዝብ የራሱን እድል ራሱ እንዲወስን መደገፍ በቂ እያለ ህወሓት ለኤርትራ ነፃነት መቀስቀሱ ተቃውሞ አስነስቶ ነበር፡፡

ገብሩ ከሚያነሳው የጥናት ጥያቄ ወይም የጥናት አስፈላጊነት ግንዛቤ ይልቅ ህወሓትን ለኤርትራ ነፃነት እንዲታገል ያደረጉት ምክንያቶች፣ መለስ ኤርትራን ለማስገንጠል የነበረው ፍላጎት፣ ህወሓትን ሙሉ ለሙሉ ለመቆጣጠር መቻሉና ህወሓት ዴሞክራሲያዊ ድርጅት አለመሆኑ ናቸው፡፡ በተሓህት/ህወሓት ውስጥ በፅሁፎች የፃሓፊው ስም እንዳይገለፅ መከልከሉና የግለ-ሰብ ፅሑፎች በድርጅት ስም መውጣታቸው፣ ባንድ በኩል ፃሓፊው በሃላፊነት እንዳይጠየቅ መከላከያ ሲሆን በሌላ በኩል ፅሑፉ በድርጅቱ ስም እንደ ማስተማሪያ አባሎች ይቀሰቀሱበት ስለነበረ ፅሑፉን መቃወም ድርጅቱን እንደመቃወም እንዲታይ ስለተደርገ ያንድ ሰው ፍላጎት ሁሉም እንዲቀበሉት የሚያደርግ አሰራር ነበር፡፡

## የትግርኛ ተናጋሪው ህዝብ መከፋፈል

ኢትዮጵያንና ኤርትራን ለማገናኘት ከሚጠቅሙ ድልድዮች ትልቁ ትግርኛ ተናጋሪው ህዝብ ስለሆነ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን እንድትተሳሰር ትልቅ ሚና ተጫውቶ ነበር፡፡ ከትግርኛ ተናጋሪው የፈለቁ አምባገነኖች ግን ህዝቡን ኤርትራ ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ተጠቅመውበታል፤ ደም አቃብተውታል፤ በጉርብትና ደረጃም በሰላም እንድይኖር አድርገውታል፡፡ ይህ ሁኔታ መቀየር አለበት፤ በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል ሰላም እንዲሰፍንና መቀራረብ እንዲጠነክር በተለይ ከጦርነቱ በሁዋላ በትግርኛ ተናጋሪው ህዝብ ውስጥ የተከሰተው አለመተማመን መወገድ አለበት፡፡

---

6 መለስ ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል እንደ ሻዕቢያና ጀብሃ መሪዎች ቢታገልም፣ መለስ ሻዕቢያን መጠምዘዝ ስለማችልና ሻዕቢያ ከደርግ ጋር እንዳይታረቅም ስላሰጋው ሻዕቢያን ለማዳከም ሁለት ሙከራዎች አድርጓል፡

1ኛ በ1974 የቀይ ኮከብ ዘመቻን ለመመከት የህወሓት ሰራዊት ሻዕቢያን እንዳይረዳ ተከራክሮ፣ በዛን ጊዜ ገና ስልጣን ያልጠቀለለበት ጊዜ ስለነበረ በድምፅ ተሸንፏል፡፡ መለስ ቢሳካለት ኖሮና ሻዕቢያ ቢዳከም የህወሓት መዳከምም አይቀርም ነበር፡፡ ገብሩ በገፅ 108 ላይ አረጋዊ ለስብሓት የፃፈውን ደብዳቤ በሚመለከት ወደ ሻዕቢያ ሃይል መላኩ ትክክል እንደነበረ መከራከሩን ሲገልፅ የፃፈውም ደብዳቤ ሃይል መላኩን የሚቃወሙትን የሚመለከት እንደነበረ ያሳያል፡፡

2ኛ በ1977 ህወሓትና ሻዕቢያ ከተጋጩ በሁዋላ የኤርትራ ህዝብ በሻዕቢያ ምትክ ሌላ በማርክሰ-ሌኒንነት የሚመራ 'ዴሞክራሲያዊ ድርጅት' እንዲመሰርት የህወሓት አባሎች ኤርትራውያንን እየሰበሰቡ እንዲቀሰቅሱ አድርጎ ነበር፡፡ እንደነ ሳግምና ስሙር ቅልፁም ያሉ የኤርትራ ድርጅቶች (አውሮፓ ለነበሩት በገንዘብ ጭምር) ከህወሓት እርዳታ ይሰጣቸው ነበር፡፡ መለስ ብህወሓት ስልጣን ጠቅልሎ ስለነበረ የውስጥ ተቃውሞ ባያጋጥመውም ኤርትራውያን ስላልተቀበሉትና ሻዕቢያም በሱ ስትራተጂ ያልተማከለ የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ ደርጅቶች ኤርትራ ውስጥ እንዳይንቀሳቀሱ ስለከለከለ አላማው አልተሳካም፡፡

## 2. የግፍ ግድያዎች፣ የፈጠራ ቀውሶችና ኢዴህ

ገብሩ የ1969 ቀውስ በሚል ገልፆታል፡፡ በተሓህት/ህወሓት እንደ ድርጅታዊ ቀውስ፣ በትግርኛ ሕንፍሽፍሽ (ብጥብጥ) አንዳንድ ጊዜም የአንጃ እንቅስቃሴ እየተባሉ በድርጅቱ ውስጥ እንዳጋጠሙ ችግሮች የሚገለፁ የታሪክ ምእራፎች አሉ፡፡ እኔ እንደታዘብኩት ከባድ ችግሮች ስላጋጠሙ ሳይሆን እንደመፍትሄ የተወሰዱትን እርምጃዎች ትክክል መስለው እንዲታዩ ጥቃቅን ችግሮች ተጋንነው እንዲገለፁ ወይም በስልጣን ላይ የነበሩት ሰዎች ወንጀል ስለፈፀሙ በሚጠየቁበት ጊዜ ከሳሾቹን በመቅጣት ተካሳሾቹን የሚያወድሱባቸው አሻጥሮች ነበሩ፡፡

ገብሩ በድርጅቱ "ቀውስ" በመባል የተለመደውን አጠራር ሳይቀይር ተጥቅሞ "ከሳሾችን በመወንጀል" (ገፅ 90) ብሎ ሲገልፀው ወንጀሉ ክስ ወይም ቅሬታ ማቅረብ ሳይሆን ከሳሾቹን መወንጀል እንደሆነ ያመለክታል፡፡ መነሳት የሚገባቸው ቅሬታዎች ያነሱ አባላት ነበሩ፤ በስልጣን ላይ የነበሩት ሰዎች ደግሞ ቅሬታዎቹ፣ ከሳሾቹ እምነት በሚጥሉበት አካል እንዲጣሩም እንዲታወቁም ስላልፈለጉ ቅሬታ ያነሱት ድርጅቱን ለማፍረስ የሚንቀሳቀሱ አውራጃውያን አስመስለው በመግለፅ ቅስቀሳዎች አካሄዱ፤ እርምጃዎች ወሰዱና ታሪኩንም አጣምመው ፃፉ፡፡ በህወሓት አባላት ላይ የውሸት ክስ የመሰረቱት ሰዎች ቆይተው እነ ቅንጅትን በዘር ማጥፋትና በክህደት ያስከሰሱት ሰዎች ናቸው፡፡ ጥያቄው ቅንጅትና አብረውት የተከሰሱት ነበሩ ወንጀለኞች ወይስ ወንጃዮቻቸው? የሚል ነው፡፡

***ታጋዮችን አታልሎ መግደል የፈጠረውን ቅሬታ*** መጥቀስ እውነታው ምን እንደነበረ ለመረዳት የሚጠቅም ይመስለኛል፡፡ ይህን ጉዳይ ለማንሳት የፈለግኩበት ምክንያት ገብሩ ታጋዮች የሰብአዊ መብት ጥያቄዎች እንዳነሱ በጠቀሰው ሃሳብ ሊካተት ቢችልም የንፁህ ሰዎች ህይወት መቅጨት ወንጀል በጥቅል ሲታለፍ ግልፅ ስለማይሆን ነው፡፡ ከገብሩ ጋር በስልክ ተነጋግረን ታጋዮችን አታልሎ መግደል አስከትሎት የነበረውን ቅሬታ አስታውሸው መጥቀሱን ረስቶት እንደነበረና መጠቀስ እንደሚገባው አምነዋል፡፡

ስለዚህ እንደ ችግር/ቀውስ ከሚገለፁት አራት ክስተቶች አንዱን ትንሽ ዘርዘር አድርጌ እገልፀዋለሁ፡፡ ከዛ በፊት ግን አራቱ ቀውሶች (ገብሩ የቀውስ ርእስ የሰጣቸው ለሁለቱ ነው) እንደተፈቱ ከተገለፀ በሁዋላ የተከተሉት ለውጦች ባጭሩ ማቅረብ፣ ስልጣን የነበራቸው ሰዎች የፈለጓቸውን ውጤቶች ለማግኘት 'ቀውሶች' እያሉ የሚጋንኑበት ምክንያት ለመረዳት ፍንጭ የሚሰጥ ይመስለኛል፡፡

ከነዚህ 'ችግሮች' 1ኛው ከሸሬ የታገሉ አርሶ አደሮች (እንደዛ ይጠራሉ እንጂ አርሶ አደሮችም አልነበሩም) በስልጣን ላይ የነበሩትን ተማሪዎች ለመግደል ፈልገው እንደነበረ የሚገለፀው ነው፡፡ የመፍትሄው ውጤት ገሰሰው አየለን (ስሑልን) ማግለልና ራሱ ከስልጣን እንዲያገል ማድረግ ነበር፡፡ ከዛ በሁዋላ ገብሩ እንደገለፀው የስብሓት ሚና ከፍ እያለ ሄደ፡፡ የ2ኛው (ይኸን እዘረዝረዋለሁ) ቀውስ መፍትሄ ያስከተለው ውጤት ከማእከላዊ ኮሚቴ ውጭ የሆኑት ታጋዮች በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የራሳቸውን ሃሳብ እንዳይሰጡና እርስ በርሳቸው እንዳይተማመኑ፣ ትእዛዝ እየተቀበሉ ብቻ እንዲፈፅሙ ያደረገ (መለስ ለካደሬዎቹ ባሰራጨው ፅሑፍ መሰረትም ታጋዮቹ ከዛ በሁዋላ ቃል በቃል passive እንደሆኑ ይገልፃል)፣ ባጭሩ የታጋዮቹ የፍትሕና የእኩልነት መንፈስ የገደለና የማእከላዊ ኮሚቴ አባሎች ካለ ምንም የተራ አባላት ተቃውሞ የፈለጉትን የሚያደርጉበት ሁኔታ የፈጠረ ነበር፡፡ 3ኛው አረጋዊ በርሀን እና ግደይ ዘርአፅዮንን ከስልጣን በማስወገድና ተክሉ ሃዋዝን በመግደል የተቋጨ ነበር፡፡ ይኸም የሚያሳየው በህወሓት ውስጥ በሃሳብ የተለየውን የማጥቃት ባህል ነው፤ በሃሳብ ተለያይቶም መቻቻል ቢኖር ኖሮ የድምፅ ብልጫ ያገኘውን ሃሳብ ተግብረው ልዩነቱን ለጥቃት ሳይጠቀሙበት ሊቀሩ ይችሉ ነበር፡፡ ከዛ በላይ ግን እርምጃው ከቡድናዊ አምባገነንነት ወደ ግለ-ሰብ (መለስ) ፈላጭ ቆራጭነት የተደረገውን ሽግግር አስከተለ፡፡ 4ኛው እነ ገብሩ ከድርጅቱ የተባረሩበትና ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት ጠንካራ አቋም የነበራቸው ተመንጥረው ወጥተው ለሉአላዊነት አስተማማኝ አቋም የሌላቸው ሰዎች ህወሓትን ከዛም በላይ ኢትዮጵያን የተቆጣጠሩበት ሁኔታ አስከትሏል፡፡ አፋኝ ድርጅቶች (ለምሳሌ፣ ናዚዎች፣ ፋሽስቶች፣ ቦልሸቪኮች በተለይ በስታሊን ስር፣ ስልጣን የያዙ አክራሪ የሃይማኖት ድርጅቶች ወዘተ..) አባሎቻቸው ነፃ ሆነው፣ በግልፅ ተወያይተው አቋም እንዲወስዱ ስለማይፈቅዱ አጥቂና ተጠቂ ያፈራሉ እንጂ እንደ ድርጅት አይከፋፈሉም፡፡ የህወሓት አመራርም አፋኝ ስለሆነ ህወሓት በድርጅት ደረጃ አልተከፋፈለም፡፡

በህወሓት ውስጥ አመራሩ በ1969/70 በተራ አባሎች ላይ ያካሄደው ዘመቻ ታጋዮች ትእዛዝ

ተቀባዮች፣ ከላይ ከተነገራቸው ሃሰብ ውጭ የተለየ ሃሳብ መግለፅ የሌለባቸውና የተነገራቸውን የማይቃወሙ እንደሰለጠነ የቤት እንስሳት የተወሰኑ ድርጊቶችን የሚፈፅሙ ሆነው ስለታነፁ እነ አረጋዊ ሲወጡና ከነ ገብሩ ጋር ወደ ግማሽ የሚጠጉ የማእከላዊ ኮሚቴ አባሎች ሲባረሩ፣ የህወሓት አባላት ሳይገባቸው እንደ ገደል ማሚቶ የተነገራቸውን ማስተጋባትና ማጨብጨብ እንጂ መጠየቅና መቃወም አልነበረም፡፡ ተራ ታጋዮቹ በነፃነት ሃሳባቸውን መግለፅ የሚችሉ ቢሆኑ ኖሮ እነ አረጋዊና እነ ገብሩ አይባረሩም ነበር፡፡ እነ አረጋዊና እነ ገብሩም ሌላው ሲጠቃ ከተጠቂው ጋር አልተሰለፉም እነሱ ራሳቸው ሲጠቁም ከነሱ ጋር የመሰለፍ መብት ያለው አልተገኘም፡፡

ለአራቱም 'ቀውሶች' ለተባሉት ሂደቶች 'መፍትሄዎች' የተባሉት እርምጃዎች ያስከተሏቸው ውጤቶች የተወሰኑ ሰዎች ስልጣን መጨመርና ያፈና መባባስ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ያህል ብዙ ሰዎች የሚያውቁትን 4ኛውን 'ቀውስ' ብንወስድ የ'ቀውሱ' መንስኤ ጦርነቱ እንደነበረ አሻሚ አይመስለኝም፡፡ የተባረሩት ሰዎች በጦርነቱ ጊዜ የሚያስወነጅላቸው አቋም ባያራምዱም ከመለስ ጋር ቅራኔ ውስጥ የገቡት በዛ አቋማቸው ምክንያት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የተባረሩት በዛ አቋማቸው ምክንያት ነው ከተባለ አሳማኝ ስላልሆነ ሌላ የማጭበረበሪያ ተረት፣ የቦናፓርቲዝም ተረት ካለቦታው እንዲገባ ተደረገ፡፡ የቦናፓርቲዝም ዋና መገለጫም የቡርዣው መደብ ከቦናፓርት ጋር ተባብሮ ተራ በተራ መጀመሪያ ላብ አደሩን ከዛ ንኡስ ከበርቴውን ካስጨፈጨፈ በሁዋላ በአርሶ አደሩ ለተመረጠው ቦናፓርት ስልጣኑን ማስረከቡን፣  አብዮቱ ተቀልብሶ፣ ቦናፓርት አምባነናዊ አገዛዝ መመስረቱን የሚያመለክት ነው፡፡ ቦናፓርት ወታደሩን በምግብና በመጠጥ ይደልል ነበር፣ ሙስና ልዩ የስርአቱ መገለጫ እንደሆነ ግን በጉዳዩ ሰፊ ጥናት ያደረጉ ሙህራንም (ለምሳሌ Hauke Brunkhorst[7]) አይገልፁትም፡፡

ቦናፓርቲዝም ከሙስና ጋር ሳይሆን ከፋሽዝም ጋር ተያይዞ ይገለፃል፤ ምክንያቱም ሂትለርና ሙሶለኒም ስልጣን የያዙት ህዝብን አዋናብደው ተመርጠው ነበር፡፡ ይኸን ታሪክ ትተን መለስ የፈለገው ሙስናን ለማጥፋት ወይም ለመግታት ነበር ቢባልም ቅንነት ያለው ሃሳብ ሊቀርብ አይችልም፤ ምክንያቱም ከተባረሩት አብዛኞቹ ሃብት የላቸውም፤ እነሱ ከተባረሩም በሁዋላ ሙስና የስርአቱ መገለጫ ነው፡፡ ችግሩ ሙስና ቢሆን ኖሮና መፍሄ ቢፈለግለት ኖሮ ሙስናውን ገብሩ እንደገለፀው (ገፅ 362) በገለልተኛ አካል ማጣራት ይቻል ነበር፡ ስለዚህ የማባረሩ እርምጃ ቢያንስ ፀረ ዴሞክራሲ፣ የህግ ስርአት ያልተከተለ የፈላጭ ቆራጭ የግል የቂም በቀል ድርጊት ነው፡፡ በስፖርትም አጭበርብሮ ማሸነፍ ያስቀጣል፡፡ እነ መለስ እንዳደረጉት በህዝብና አገር ጉዳይ አጭበርብረው፣ ዋሽተው፣ ስልጣንና ጉልበት ተጠቅመው የፈፀሙት ከፍተኛ የወንጀል ድርጊት ጉዳቱ በህዝብና ባገር ላይ ስለሆነ እንደዚህ አይነት አስተሳሰብና አሰራር የሚያስነውርና ተቀባይነት የሚያሳጣ ህዝባዊ ባህል መዳበር አለበት፡፡ የገብሩ ማብራሪያ ለዚህም ይጠቅማል፡፡

**የ 1969 'ቀውስ'**

የ 69 ቢባልም እስከ 1970 ነበረ፡፡ ይህን ጉዳይ ሳነሳ በግልም የሚረብሸኝ ድርጊት አለ፡፡ በ 969 ጥቅምት ወር ውስጥ የተሓህት አመራር በትግል መቀጠል የከበዳቸውና ወደ ወላጆቻቸው ለመመለስ የሚፈልጉ ታጋዮች መሄድ እንደተፈቀደላቸው ገለፀ፡፡ እኔም የነበርኩበትን ሃይል ሰብስቤ መልእክቱን አስተላለፍኩ፡፡ ለመሄድ ፍላጎት እንዳላቸው ለመግለፅ እጃቸው ካወጡ ታጋዮች ውስጥ አንድ ሃይላይ የሚባል በግምት የ 17 ዓመት ወጣት በመሄድና ባለመሄድ መወሰን ስላቃተው ማልቀስ ጀመረ፡፡

እኔ ደግሞ ትግሉን መተው መፈቀዱ እውነት ስለመሰለኝ ወጣቱን አፅናንቼ፣ ከቤተሰቡ ጋር እየኖረም መታገል እንደሚችል ከፈለገም ተመልሶ ወደኛ መምጣት እንደሚችል ነግሬ ወደ ወላጆቹ እንዲሄድ ገፋፋሁት፡፡ ወደየቤታቸው የሚመለሱት አንድ ላይ እንደሚሰበሰቡ ሰማሁ፤ ለጊዜው ቁጥራቸው አስር አካባቢ ነበር፤ አሰራሩ (ቆይቼ እንደሰማሁት፣ መኮነን ዘለለውም ከኢሳት ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ እንደገለፀው፣ እያታለሉ በመሰብሰብ መረሸኑ) ቀጥለዋል፡፡

ከጥቂት ወራቶች በሁዋላ ወደየቤተሰቦቻቸው መሄድ እንደተፈቀደላቸው ተነግሯቸው የተሰበሰቡት ወጣቶች እንደተረሸኑ ሰማሁ፡፡ እኔ መጀመሪያ ላይ ድርጊቱን ማመን ስላቃተኝ ጥያቄዬ 'ለምን ተረሸኑ?' ሳይሆን 'እውነት ተረሽነዋል ወይ?' የሚል ነበር፡፡ በፅሑፍ አላየሁም፤ በቃል ግን በድርጅቱ ውስጥ ተራ አባላት በአመራሩ ላይ ቅሬታ ከተሰማቸው ራሳቸው በመረጧቸው ግለ-ሰቦች አጣሪ ቡድን ማቆም ይችላሉ በሚል መግባባት መሠረት ጉዳዩ መጣራት ነበረበት፡፡

---

7 *Karl Marx: Der achtzehnte Brumaire des Louis Bonaparte – Kommentar,* Frankfurt (Suhrkamp) 2007

በ1969 ክረምት የድርጅቱ የፖለቲካ ኮሚቴ ሃላፊ የነበረው አባይ ፀሃየ የአንድ ሃይል አመራር የነበረነውን ጠርቶን ተሰበሰብን፡፡ አባይ ድርጅታዊ ጉባኤ የመጥራት ሃሳብ ስላለ በታጋዮች ሁኔታ እንድንነጋገር ሃሳብ አቀረበ፡፡ እኛ ሰዓረ[8] ኮሚሳር፣ አሰክሕ[9] የሃይል ምክትል አዛዥና እኔ ነበርን፡፡ በታጋዮች ውስጥ ቅሬታዎች[10] ስላሉ ቅሬታዎቹ እንዲጣሩ ሃሳብ አቀረብን፡፡ አባይ "ጉባኤውን ለመጥራት ተነሳሽነት (ተበግሶ) ያደርግነው የማእከላዊ ኮሚቴ አባሎች ስለሆን የተራ አባሎች ቅሬታ አይጣራም፣ የተራ አባሎች ቅሬታ ሊጣራ ይችል የነበረው ጉባኤ የመጥራቱ ተነሳሽነት የነሱ ቢሆን ኖሮ ነበር" ብሎ ያልጠበቅነው መልስ ሰጠን፡፡

በእግርጌው ማስታወሻ የሰዓረና አሰክሕ ማንነት የጠቀስኩትም አባይ ትርጉም አልባ ምክንያት ሰጥቶ ሊያሳምነን እንደማይችል ለማመልከት ነው፡፡ መብት ቀድሞ ተነሳሽነት ላሳየ ሳይሆን ለሁሉም እንደሆነ ስንነግረው መልስ ስላጣ፣ ዝም አለ፡፡ በስነ ስርአት ተነጋግረን ሳንስማማ ተለያየን፤ ምክንያቱም አባይ ዝም ቢልም ሃሳባችንን አልተቀበለም፡፡

ከስብሰባው ወደየነበርንበት ስንመለስ እንዳጋጣሚ ከገብሩ ጋር ተገናኝተን ገብሩ ስለ ስብሰባው ጠየቀኝ፡፡ ገብሩ ስልጣን ላይ የነበሩትን ከእኔ ቀድሞ ስለሚያውቃቸው ሲያነጋግረኝ ይጠነቀቅ ነበር፡፡ አባይ የነገረንን ስነግረው ደግሞ አባይ የተናገረው የራሱ ሳይሆን የመለስ እንደሚሆን ምክንያቱም መለስ ከውግያ ሸሽቶ ተገቢ ቅጣት አልተሰጠውም ብሎው ቅሬታ የሚያቀርቡ ታጋያች ስላሉ የቅሬታዎች መጣራት የሚያስፈራው መለስን እንደሆነ ነገረኝ፡፡ ገብሩ እንዳለው መለስ የታጋዮች ቅሬታዎች መጣራት ባይፈልግም አባይ ራሱም ቅሬታዎች እንዲጣሩ ላይፈልግ ይችላል፤ ምክንያቱም ቢያንስ ተታልለው የተረሸኑትን አባላት በሚመለከት ሁሉም ስልጣን ላይ የነበሩት ሰዎች አብረው ከወሰኑ ወንጀሉን በመፈፀም ወይም ባለመቃወም ተጠያቂዎች ናቸው፡፡ ወንጀሉ በተናጠል ከተፈፀመም ወንጀሉን የፈፀሙና ያላጋለጡ ተጠያቂዎች ናቸው፡፡

እስካሁን ድረስ ከ38 ዓመታት በሁዋላም ጉዳዩ አልተጣራም፡፡ በየዋህነት ወይም ጥቅማቸው እንዳይነካ ያለፈውን ትተን በወደፊቱ ላይ እንድናተኩር የሚገልፁ ሰዎች አሉ፡፡ ችግሩ ግን ያለፈው ወንጀል አለመጣራቱ ብቻ ሳይሆን ወንጀል የሰሩ ባለስልጣኖች ካልተጠየቁ ተመሳሳይ ወንጀሎች መፈፀም ስለሚቀጥሉ፣ እንዲያውም ግልፅነት ስለሚየስፈራቸው አፈናቸውን ስለሚያጠናክሩ ያለፈውን ማንሳት ለወደፊቱም ማሳብ መሆኑን መገንዘብ ስለሚያስፈልግ ነው፡፡

ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ በየአሃዳችን ካለ ምንም ጫና በወታደራዊ ሸንጎ የሚሳተፉ ወኪሎች መረጥን፡፡ ከተመረጡት መካከል ሰዓረ፣ ተሾመ፣ ፃድቃንና እኔ ከሩቅ ተጉዘን ስብሰባው የሚካሄድበት ቦታ ላይ ስንደርስ፣ ስብሰባው እንደተጀመረና ቅሬታዎችን የሚመለከት አጀንዳ እንደማንወያይበት ተነገረን፡፡ አባይ (ማእከላዊው ኮሚቴ ሳይስማማበት ሊሆን አይችልም) የሚፈልገውን አጀንዳ አስይዞ የማይፈልገውን አስወጥቶ ስለሄደ ስብሰባው ላይ የነበረ መሆኑን ለብዙ ጊዜ አላውቅም ነበር፡፡

ብዙ ጊዜ ሰው ሊታለል የሚችለው የሚያታልለው ሰው ቅን ሲመስለው ነው፣ እምነት የጣሉባቸውን ታጋዮች አታልለው የረሸኑ የተሓህት ባለስልጣኖች ወንጀላቸው ከባድ የሚሆንበትም ምክንያት የተጣለባቸውን እምነትና የነበራቸውን ስልጣን በመጠቀም አታልለው የንፁህ ወጣቶችን ህይወት በመቅጨታቸው ነው፡፡ እኔም ከዚያ በሁዋላ ድርጊቱን የፈፀሙት የተወሰኑ ሰዎች ሊሆኑና ሊጋለጡ እንደሚችሉ በማመኔ ተስፋ ባልቆርጥም ወንጀሉን በፈፀሙ ሰዎች ላይ ምንም እምነት አልነበረኝም፡፡

ድርጊቱ ለምን ተፈፀመ ለሚለው ጥያቄ በቂ ምክንያት ሊገኝ አይችልም፡፡ ወጣቶቹ ተገድደውም ይሁን ሳይገደዱ መረጃ ለመንግስት ሰጥተው ድርጅቱን ይጎዳሉ እንዳይባል ከዛ በፊትና በሁዋላ ሃላፊነትና የተሻለ መረጃ የያዙ ታጋዮች እያመለጡ ለመንግስት እጃቸውን ይሰጡ ነበር፡፡ በተለይ

---

8፡ ሰዓረ የሜዳ ስሙ ሲሆን ትክክለኛ ስሙ ተክሉ ሆኖ፣ ሲዳሞ ውስጥ ያደገና በባእደማርያም ወደ ዩኒቨርሲቲ የገባ ነበር፡፡ ጠበቃ ሆኖ እንደሚሰራ ሰምቻለሁ፤ የት እንዳለ ግን አላውቅም፡፡

9 ፡ አስክሕ የቤት ተሻለ ግደይ፣ የአየር ሃይል አባል የነበረ፣ የአባይ ፀሃየ የክፍል ጓደኛ የነበረና በሃምሌ 4፣ 1970 ገርሁ ስርናይ ላይ የተሰዋ ታጋይ ነበር፡፡

10 በነበርነው ሃይል ቅሬታዎች ቀርበው ስለማያውቁ አንድ ጊዜ ፃድቃን በሃይላችን ቃል በቃል "የቸርች ዲሲፕሊን" ያለን እንደሚያስመስለን ጠቅሶ በእኔ በሰዓረና አሰክሕ ላየ ሂስ አቅርቦ ነበር፡፡ ከኛ ከሆነ ብለን ሃይል ሰብስበን ቅሬታዎች እንዲቀርቡ ጠየቅን፤ ነገር ግን ቅሬታ የሚያቀርብ አባል አላገኘንም፡፡

በ1969 የመጀመሪያው አጋማሽ ወደ ከተሞች የሚሸሹ በዝተው ስለነበር፣ እኔም ድንገተኛ ጥቃት እንዳይደርስብን ለመከላከልና መሳሪያና ሰዓት ይዘው የሚያመልጡትን ለመግታት በየሌሊቱ አካባቢውን እየዞሩ የሚቆጣጠሩ ጓዶች (patrol squads) የመመደብ አሰራር ለመጀመር ተገድጄ ነበር፡፡ ከዚያ በሁዋላ አሰራሩ በሌሎች ሃይሎችም ተለመደ፡፡

ይህ አታልሎ በመሰብሰብ የመረሸኑ ጉዳይ የሚመለከት ወንጀል የፈፀመ አካል ሕግ አውጪ ሕግ አስፈፃሚና ዳኛ ሲሆን ወንጀሉና የተጎጂዎች ቁጥር እየጨመሩ እንደሚሄዱ ያሳያል፡፡ መጀመሪያ የማታለል ወንጀል ተፈፀመ፤ ቀጥሎ የግድያ ወንጀል ተጨመረበት፡፡ ድርጊቱ ቅሬታዎችን አስከተለ፣ እንዲጣራ የሚፈልጉ ድምፆች እየተበራከቱ ሄዱ፡፡ ተከሳሾቹ አስተዳደራዊ ስልጣናቸውንና የተወሰኑ ደጋፊዎቻቸውን ተጠቅመው እንዳይጣራ ከለከሉ፡፡ ተከሳሾቹ ግን በፈፀሙት ወንጀል እንዳይከሰሱ ማድረጋቸው ስላልበቃቸው ለወደፊቱም በሌሎች ወንጀሎች እንዳይከሰሱ ለማድረግ ዘመቻ ከፈቱ፡፡ ቅሬታ እንዳላቸው የገለፁትን ድርጅቱን ለማፍረስ አቅደው የተንቀሳቀሱ፣ አንጃኞችና አውራጃውያን እንደሆኑ በማስመሰል እነሱ ተጋልጠው እርምጃ ካልተወሰደባቸው 'ድርጅታችን ልትበተን ነው' የሚል ስጋት በታጋዮች ውስጥ ፈጠሩ፡፡

ጠባብ ብሄራዊነት ወደ አውራጃዊነት የማሽቆልቆል አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ያስፈራን ስለነበረ ውይይቶች እናካሂድ ነበር፡፡ ለምሳሌ በ69 አጋማሽ አካባቢ በሃይል 60 ፀድያ በሚባል ቦታ አሁን በስልጣን ላይ ካሉት ስብሓትና ሳሞራ (በዛን ጊዜ ተራ አባል የነበረ) በነበሩበት ከጠባብ ብሄራዊነት መጠንቀቅን በሚመለከት ሰፊ ውይይት አድርገን ነበር፡፡

አውራጃ ነክ መስለው ከታዩት አጋጣሚዎች አንዱ ሁለት ሃይሎች ለድርጅቱ ወደ ደቡባዊ የትግራይ አካባቢዎች መንቀሳቀስ አስፈላጊ እንደሆነና አመራሩ እንቅስቃሴውን እንዲፈቅድ መጠየቃቸው ነበር፡፡ አመራሩ ግን ሃሳቡን አልተቀበለውም፡፡ አመራሩ ጥያቄውን ካውራጃዊነት ጋር እንደተያያዘ አድርጎ ስላቀረበው ቀላሉ ነገር ወደ ውዝግብ ተቀየረ፡፡

ያንዱ ሃይል፣ የሃይል 11 አዛዥ የነበረ ሃይለ ፖርት ሱዳን (የሻዕብያ ታጋይ የነበረ) አውራጃውያን ተባልን እያለ ቅሬታውን መግለፅ ጀመረ፤ ከዛም አልፎ እንደደከመው ገልፆ እረፍት እንዲሰጠው ጠየቀ፡፡ በዛ ምክንያት ታሰረ፡፡ የእስር ቤቱ ሃላፊ (ገብረዮሃንስ፣ አሁን በስዊዘርላንድ የሚኖር) ከነ ሃይለ ፖርት ሱዳንና ግርማይ ባህሊ ጋር ከእስር ቤቱ አመለጠ፡፡ ስለዚህ ምናልባት ከተመክሮ ማነስ በቀላሉ ሊፈታ የሚችል የሃሳብ ልዩነት በውይይት ስላልተፈታ ያውራጃዊነት ችግር እንደሆነ ወሬው ተዛመተ፡፡

በመጨረሻ በጥቂት የምርጫ አዘጋጅ ኮሚቴ አባላት የተካሄደው የምንጠራ ዘመቻ በተወሰነ ጥፋት፣ አካባቢ ወይም አስተሳሰብ ያነጣጠረ ሳይሆን በአመራር፣ አሰራር፣ አመዳደብ፣ ድርጅታዊ ድክመት ወይም ባመራሩ ላይ በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ ቅሬታ መግለፅና በቡድን  መታየት የሚመለከት ነበር፡፡

ብዙ አባላት አምነውበትም ይሁን ራሳቸው እንዳይጠረጠሩ ታማኝነታቸውን ለመግለፅ ጥቃቅን ነገሮች እየለቃቀሙ እርስ በርስ ወደ መወነጃጀል ገቡ፡፡ መተማመን ጠፋ፤ ከዛ በሁዋላም አልተመለሰም፡፡ ስልጣን ባላቸው ሰዎች ላይ ቅሬታ እንዳላቸው የገለፁ አባሎች ታጋዮችን ባመራሩ ላይ እምነት አሳጥተው ድርጅቱን ለማፍረስ እንደተንቀሳቀሱ ስለተገለፀ ስልጣን የነበራቸውን ሰዎች መፍራትና በእነሱ ላይ ሂስ አለማቅረብ የታማኝነት መገለጫ ሆነ፤ ከዛ በሁዋላ የበላይ የበታችነት እየሰፋ ሄደ፡፡

በገለፅኩት ሂደት እኔ በነበርኩበት ያገጠመኝ እንደሚከተለው ነበር፡፡ በ1970 ታህሳስ አካባቢ ማይ ምሻም በሚባል ቦታ ከአዘጋጅ ኮሚቴ አባላት አርከበ መጥቶ ቅሬታዎችን ለማጣራት እንደሚፈልግ ጠቅሶ ሃይል እንድሰበስብለት ጠየቀኝ፡፡ ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት አባይ ቅሬታዎች እንዲጣሩ እንደማይፈልግ፣ በወታደራዊው ሸንጎም ቅሬታዎችን የማጣራት ጉዳይ እንደ አጀንዳም እንዳይቀርብ እንደተደረገ አውቅ ስለነበር አርከበ የተናገረው እውነት እንዳልሆነ ቢገባኝም ራሱ ከተናገረው ሳልወጣ በዴሞክረሲያዊ ማእከላዊነት አሰራር በአሃዳችን  መፍትሂ ያላገኘንለት ቅሬታ ስለሌለ ስብሰባ እንደማያስልግ ነገርኩት፡፡

አርከበ ያቀረበውን ሃሳብ ስላልተቀበልኩት በትእዛዝ መልክ እንዲነገረኝ ወይም በበኩሉ እንደሞከረ ለማሳወቅ የነገርኩትን ለአባይና ስዩ ነገራቸው፡፡ አባይና ስየም እኔ ያልኩትን ሃሳብ ስለተቀበሉ

(ለጊዜው) ስብሰባው ቀረ፡፡ አርከበ ያሰበው ምንጣራ እንጂ እንደተናገረው ቅሬታዎችን ማጣራት እንዳልነበረ ራሱም ስለሚገልፀው (እጠቅሰዋለሁ) አባይና ስየም ምናልባት አቀራረቡ ካልተጣመመባቸው በስተቀር አርከበ ስልጣን ስላልነበረው የማእከላዊ ኮሚቴ እቅድ በመፈፀም ላይ እንደነበረ ሳያውቁ ሊቀሩ አይችሉም፡፡ በነበርኩበት ሃይል ቅሬታዎች እንዳልነበሩ የተናገርኩት እውነት እንደሆነ ግን አባይና ስየ ያውቁ ነበር፡፡

ከግማሽ አመት በላይ ቆይቶ ግንቦት 1970 ላይ አርከበ ወደነበርኩበት ሃይል መጣ፡፡ ሓጐስ ሃይለስላሴ የሚባል በነበርኩበት ሃይል የነበረ ታጋይ ወደ ሜዳ ከመውጣቱ በፊት ግደይ ዘርአፅዮን እና ስየ ከድርጅቱ መውጣታቸውን ማውራቱን የሰማ አንድ ገብረገርግስ የሚባል አባል ለምስክርነት ይዞ እንደመጣ፣ ነገረኝ፡፡ አርከበ ስለ ሓጐስ የነገረኝ ሓጐስ ሲመደብ ተነግሮኝ ስለነበረ አውቀው ነበር፡፡ ሓጐስ አንድ አመት ያህል በውግያዎች እንደ ሌሎች እየተካፈለ ስለቆየ ሊሰዋም ይችል ነበር፡፡ አርከበ መጋለጥ ያለበት ትልቅ ነገር እንዳገኘ ለማረጋገጥ ምስክር ይዞ ስለመጣ ተሰበሰብን፡፡ ስብሰባ ላይ ገብረገርግስ 'ብለሃል' ሲል ሓጐስ 'አላልኩም' አለ፡፡

ሌሎች አባሎች ለድርጅቱ አደገኛ ሁኔታ የተፈጠረ መስሏቸው የሆነ ያልሆነውን ጥቃቅን መቀባጠር ጀመሩ፡፡ የሓጐስ ጉዳይ በሓለዋ ሰውራ (አብዮት ጥበቃ) እንዲጣራ ተወሰነ፡፡ የአውራጃ ነገር አልተነሳም፡፡ሓጐስ ከሄደበት አልተመለሰም፡፡ በስብሰባው ውጥረትና አለመተማመን ስለሰፈነ አንድ ምንም አይነት ሂስ ያልቀረበበት ተካ የሚባል የመቶ መሪ በዛው ቀን ሌሊት ሸሽቶ አመለጠ፡፡ አንድ የሰዎች ስብስብ መጨነቅ ከጀመረና ነፃነት ካልተሰማው ሰክኖ ሊወያይና ሚዛናዊ ውሳኔ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ታጋዮቹ ያንድ አባል ክስ ይጣራ ሲሉ ግን አባሉ ይረሸን ማለታቸው አልነበረም፡፡

ቅሬታዎች ካስነሱት ምክንያቶች ውስጥ ዋናዎቹና ተጨባጭ ማስረጃዎች የነበሯቸው የግድያ ወንጀሎች ቢሆኑም ስለ ቅሬታዎች የሚያወሩት ሓንፈሽቲ (ብጥብጥ ፈጣሪዎች/አንጃኞች) አውራጃውያን እንደሆኑና ከኢዴህ ጋር በተደረገው ጦርነት ብዙ የተሓህት አባላት ለደርግ እጃቸውን የሰጡበት ምክንያት አንጃኞቹ በተሓህት አመራር ላይ እምነት ስላሳጧቸው እንደሆነ በቅስቀሳ መልክ ይነገር ነበር፡፡ ገብሩ በመፅሓፉ ቅሬታዎች ያነሱት፣ የተቀጡና ድርጅቱን ጥለው የወጡት ከተወሰኑ አውራጃዎች ብቻ እንዳልሆኑ በማስረጃ አስደግፎ (ገፅ 89) ከጠቀሰ በሁዋላ ግን ስብሓትም ትክክል እንደሆነ አምኗል፡፡ ሆኖም ስብሓት አንዱን ስህተት ተቀብሎ ሌላ ስህተት በመጨመር ሲያበላሸው ከተወሰኑ አካባቢዎች የመጡ የሚለውን በፈሪዎች ተክቶታል፡፡

ወደ ከተሞች ሄደው እጃቸውን የሰጡ እንኳን የፈሩ ነበሩ ሊባል ቢችል እየታገሉ ቅሬታ ያቀረቡትን አይመለከትም፡፡ ስብሓት የፈሩ የሚላቸውን፣ ማንን የፈሩ? የሚለውን ጥያቄ በመመለስ ከፋፍለን ልናያቸው እንችላለን፡፡ በድርጅቱ ውስጥ ግድያዎች ስለሚፈፀሙ ቅሬታ የተሰማቸው አመራሩን ቢፈሩ አያስገርምም፤ ምክንያቱም ሳያስቡትና ራሳቸውን የመከላከል እድል ሳያገኙ እንደ ጠላት ባላዩዋቸው ጓዶቻቸው የሚገደሉ ከሆነ ፍትሕ ባለመኖሩ ተስፋ ቆርጠው ቢሸሹም አያስገርምም፡፡ ጉዳዩ ግን ስለሸሹት ሳይሆን ደፍረው ቅሬታዎች ስላቀረቡት ነው፡፡

የፈሩት ኢዴህን ከሆነ ደግሞ አመራሩ እንደነ አረጋዊና ስብሓት በነበሩበትና ከሓይሎች አመራርም ጥቂቶች በነበርንበት በዓዲ ነብሪ ኢድ ፍቕረ (የሓሎም ወንድም) ቤት በ69 መጋቢት መጀመሪያ ላይ ተሰብስበን፣ በሰራዊት ብዛት እንዲሁም በትጥቅ ብዛትና ጥራት ከኢዴህ በጣም እንደምናንስ እናውቅ ስለበረ እየከፋፈልን እንጂ ፊት ለፊት መጋጠም እንዳማያዋጣን ተስማምተን ነበር፡፡ መጀመሪያ ላይ እንደተስማማነው ስላላደርግን ከፍተኛ መስዋት ከፈልን[11]፡፡ ኢዴህ ገጠሮች ላይ ቢያተኩር ብዙ ቦታዎችን መቆጣጠር ይችል ነበር፡፡ተሓህትም ኢዴህ ከተሞችን ለመቆጣጠር እንደሚቸኩል በቅድሚያ ብያውቅ ኖሮ ኢዴህ ወደ መንግስት ጦር ሰፈር ምሽጎች እንዲገባ ቢያሳልፈው (ኢዴህ በውግያ ተሓህትን ጥሶ ማለፉም በመንግስት ሰራዊት ክፉኛ መጎዳቱም አልቀረም) የተሓህት መስዋእት ይቀንስ ነበር፡፡

---

11 በነበርኩበት ሃይል 60 ሶስታችን የሓይል አመራር የነበረነው በጥይት ተመታን፡፡ ኮሚሳር የነበረው ሓጎስ (ገብሩ) ምክትል አዛዡ ከበደ ነጋሽ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰዋችብን ሴት ታጋይ ልእልቲ ሃ/ማርያም እነደዚሁም ብዙ ጠንካራ ታጋዮች በቆራጥነት ተሰዉ፡፡ ከበደ ነጋሽ እኔ ብዙ ደም ሲፈስብኝ ስላየ ለሃኪማችን ተኽለ የሚፈሰውን ደም እንዲያቆምልኝ ነገሮ "ስነ ስርዓት" ብሎ እኔን ለመተካት በድፍረት ገብቶ ስለተሰዋ በክብር አስታውሰዋለሁ፡፡ ከሃይላችን ወደ ከተማ ሸሽቶ እጁን የሰጠ ገብራይ ጃሌ የሚባል ታጋይ ብቻ ነበር፤ ከጥቂት ሳምንታት በሁዋላ ተመልሶ መጣ፤ እኛም ሳይቀጣ ትግሉን እንዲቀጥል ስለተስማማን ተቀበልነው፡፡

ብዙ የተሓህት አባሎች ቆይተው የፃሩም ጭምር ስላልተነገራቸው፣ አመራሩ አስቀድሞ አቅሙን እንደገመገመና ከኢዴህ ጋር ፊት ለፊት ግጥሚያ ላለማድረግ እንደተስማማ አያውቁም፡፡ በዚህ ምክንያትና መጀመሪያ ላይ ከፍተኛ መስዋእት ስላጋጠመ በተጋዮች ውስጥ 'ሊያሰጨርሱን ነው' የሚል ስጋት ሰፍኖ ነበር፡፡ ብዙ አባሎች ተማምነው አብረው የሚሸሹበት ሁኔታ ተከስቶ ነበር፡፡ የሽሽቱ ምክንያት በዋናነት ቅስቀሳ ሳይሆን በተጨባጭ የሚታይ የመስዋእት መብዛት ነበር፡፡ በድርጅቱ አመራር የተጠቁት ቅሬታቸውን የገለፁት እንጂ የሸሹት አልነበሩም፤ ምክንያቱም የሸሹት አምልጠዋል፡፡

ቅሬታቸውን የገለፁትን በማስረዳት ፈንታ ለሽሽቱ ምክንያት እንደነበሩ መግለፁ፣ እነሱን መፈረጁ፣ የነሱን ቃላት ለቃቅሞ ማጋነኑና ድርጅቱ በእነሱ ምክንያት አደጋ እንደተደቀነበት ማራገቡ እንደዚሁም ቅሬታ ያልገለፁትንም ማሸማቀቁ ቅን አሰራር አልነበረም፡፡ ይህ፣ ድርጅቱ አደጋ እንደተደቀነበት በመቀስቀስ፣ ስጋት በማሰፈንና ኢፍታሃዊ እርምጃዎች በመውሰድ የተፈፀመ አሰራር በድንገት ወይም እንዳጋጣሚ አንድ ጊዜ ብቻ የተከሰተ ሳይሆን የሚደጋገም ነበር፡፡ ስለዚህ መደጋገሙ በእቅድ የሚሰራ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በዚህ መሰረት በ1969/70 ድርጅቱን ለማፍረስ አውራጃውያን/አንጃኞች እንደሚነቀሳቀሱ ተገለፀ፤ በ1977 እነ አረጋዊን ከስልጣን ለማስወገድ ድርጅቱ እድገቱን አቁሞ ከነበረው እድገት እያሽቆለቆለ በመውደቅ ላይ እንደነበረ ተገለፀ፤ በ1993 እነ ገብሩን ለማባረርና ከተባረሩም በሁዋላ እነ ስየን ወደ እስር ቤት ለመወርወር ባገሪቱ ላይ የሙስና አደጋ እንዳንጀዣበበ ተነገረ፡፡ የድርጅቱ አመራር በፈጠራ ወንጀል አባላትን ሲያጠቃ ከመጀመሪያው ማረም ስላልተቻለ ማንም ኢትዮጵያዊ የዚህ አሰራር ሰለባ ሊሆን እንደሚችል ተደጋግሞ ታይቷል፡፡

የተቃዋሚ ድርጅቶች አባሎችና ጋዜጠኞች በሽብርተኝነት የሚወነጀሉት በዚህ ስልት ነው፡፡ ይህ ገብሩ በመፅሐፉ ያነሳው አሰራር እንደ ተራ ነገር መታለፍ የለበትም፤ አሰራሩ ማለትም በፈጠራ ውንጀላዎች ዜጎችን ማጥቃቱና ተበዳዩን ደጋግሞ መጉዳቱ ለብዙ አመታት የቆየ ከህወሓት/ኢህአዴግ መገለጫዎች አንዱ ስለሆነ ሁሉም ለፍትህና ለዴሞክራሲ የቆሙ ኢትዮጵያውያን ልዩ ትኩረት ሊሰጡት፣ ሊያጋልጡትና ሊያወግዙት ይገባል፡፡ መንግስታዊ ስልጣን የያዘ አካል የዜጎችን መብት በመጠበቅ ፈንታ ዜጎችን ብውሸት ሲወነጅል፣ በትእዛዝ መስክሮች ሲያሰማራ፣ በራሱ ዳኞች የሚፈልገውን ሲያስወስንና አስሰቃቂ ቅጣት ሲፈፅም ለዜጎች በጠላት እጅ ከመውደቅ የተለየ አይደለም፡፡

ኢዴህን በሚመለከት የጠቀስኩት አንድ ነጥብ በተሓህት ላይ ከዚያ በፊት በዚያ መጠን አጋጥሞ የማያውቅ ጉዳት እንደደረሰና በዛም ምክንያት ሸሽተው እጃቸውን ለደርግ የሰጡ ብዙ አባሎች እንደነበሩ፤ የተሓህት አመራር ግን ሽሽቱን የድርጅት ውስጥ ጠላት ያስከተለው ችግር አስመስሎ ያልሸሹትን ለመጉዳትና ለማሸማቀቅ እንደተጠቀመበት ነበር፡፡ ስለዚህ ተሓህት ከኢዴህ ጋር በመዋጋቱ ምክንያት የደረሰበት ችግር የመስዋእትና ሽሽት መብዛት እንጂ የሚያሰጋ የውስጥ ብጥብጥ እንዳጋጠመው የተወራው ቅሬታዎች የነበሯቸውን አባሎች ለማጥቃት የታቀደ ማጋነን ነበር፡፡ ቅሬታዎች ከመግለፅ አልፈው ትእዛዝ አንቀበልም ያሉ፣ በቡድን አድማ ያስነሱ ወይም ሆን ብለው ድርጅቱን የጎዱ አባሎች አልነበሩም፡፡

ኢዴህ የመሬት ከበርቴውን ስርአት ለመመለስ ሲሞክር ተሓህት "መሬት ላራሹ" የሚለውን መፈክር መሬትን በማከፋፈል ይተገብር ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በሁለቱ ድርጅቶች መካከል የነበረው ቅራኔ የሚታረቅ አልነበረም፡፡ ገብሩ ተመልሶ አስቦበት ደርግን ለማጥቃት ከኢዴህ ጋር የመተባበር ጥያቄ በሚመለከት አስተያየት መስጠቱ የሚያስገርም አይደለም፡፡ የኢዴህ የበላይ መሪዎች የነበሩት የታሪክ ሂደት ተገንዝበው የመሬት ከበርቴ ስርአቱን መፍረስ በወቅቱ ባይቀበሉም እንደ የደርግና የህወሓት መሪዎች አረመኔያዊ የጭካኔ ድርጊት እንዳልፈፀሙ ይታወቃል፡፡ በመለስተኛና ዝቅተኛ አመራር የነበሩ የኢዴህ አባሎች ግን ህግና ስነ ስርአት እንዲያከብሩ የስርአቱ መለወጥም እንዲቀበሉ መጠበቅ ይከብዳል፡፡ ህዝቡ ከደርግ በላይ ኢዴህን ይፈራና ስለሚፈራቸውም፣ ከመብቶቹ ውስጥ በህይወት የመኖር መብቱን ስለሚስቀድምና ለዘመናት የሚያውቀው የመሬት ከበርቴ ስርአት ሊወገድ እንደሚችል ስላላመነ የኢዴህ ደጋፊ መስሎ ለመቅረብ ይገደድ ነበር፡፡ ልኡል ራስ መንገሻን የሚደግፍም የህዝብ ክፍል ነበር፡፡

ገብሩ፣ ከደርግ ጋር በመተባበር ኢዴህን ለማጥቃት አረጋዊ ከደርግ ባለስልጣናት መነጋገሩን ተክሉ ሃዋዝ ነገሮት እንደነበረ ገልጿል፡፡ እኔ ደግሞ ደርግ እንደ ስርአት አይቀጥልም ኢዴህ የመሬት ከበርቴ ስርአቱን መልሶ ማቋቋም ከቻለ ግን በቀላሉ አይፈርስም የሚል እምነት ስለበረኝ አንድ ጊዜ ስልታዊ ግንኙነታችን ከደርግ ጋር ሆኖ በቅድሚያ ኢዴህን ማጥፋት ይሻላል የሚል ሃሳብ አቅርቤ

ነበር፡፡ አስገደ፣ አረጋዊ ከደርግ ጋር እየተነጋገረ መሆኑን ሲነግረኝ የተወሰነ ነገር መኖሩን ስላላውቅሁ ያልጠበቀኩት መልስ ሆነብኝ፡፡ ሁለታችንም ከድርጅቱ ከወጣን በሁዋላ አረጋዊን ጠይቄው ካንድ መኰንን ጋር ተነጋግሮ እንደነበረና እንዳልተሳካ አረጋግጦልኛል፡፡

## 3. ተሓህትና ኢህአሠ ሶበያ ላይ ለምን እንደተዋጉ

ተሓህትና ኢህአሠ ሶበያ ላይ ያደረጉት ውግያ በሚመለከት ብዙ ፀሓፊዎች የተለያዩና ተቃራኒ ድርጊቶች ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ ገብሩ ኢህአሠ በአንድ የተሓህት ሃይል ላይ ተኩስ እንደከፈተ ሲገልፅ (ገፅ 76) አቶ አስማማው አንዲት የህወሓት ሃይል አይረ ወንዝ ላይ አድፍጣ በኢህአሠ ላይ ተኩስ እንደከፈተች እሱም እዛው እንደነበረ ይገልፃል(ገጽ 241[12])፡፡ የተፈፀሙና፣ እንደተፈፀሙ የሚገለፁ ድርጊቶች፣ የድርጊቶች ቅደም ተከተልና ቀኖችና ሰአቶች በሚመለከት 6 ሰዎች የፃፏቸውን መፃሕፍት አንብቤ እኔ እዛው ስለነበርኩ ከማውቀው ጋር ሙሉ ለሙሉ የሚስማማ አላገኘሁም፡፡ ስለዚህ በያንዳንዱ ላይ አስተያየት ከምፅፍ ገብሩ ከገለፀው ጋር በማያያዝ የማውቀውን እገልፃለሁ፡፡

በ1970 በየካቲት ወር መጀመሪያ አካባቢ ሃይላችን፣ ’ሓይሊ 30’ ወደ ዓጋመ፣ ማለት ኢህአሠ ወደሚንቀሳቀስበት አካባቢ ከሄድን በሁዋላ በሃይል ስብሰባ ላይ እኛ በኢህአሠ ላይ ጦርነት መጀመር እንደሌለብን እና ትንኮሳም (ከዚያ በፊት በሁለቱም ድርጅቶቸ መተነኳኰስ ስለነበረ) ማቆም እንዳለብን ሃሳብ አቀርብሁ፡፡ በዝርዝር ተወያይተን በሙሉ ድምፅ ተስማማን፡፡

ሆኖም ኢህአሠ ውሳኔያችንን እንዲያውቅ አላደረግንም፤ቢያውቅም ኖሮ ምን ያደርግ እንደነበረ አላውቅም፡፡ ከውሳኔው በሁዋላ የወሰንነውን ለመፈፀም ሞክረናል፡፡ ትንኮሳ ስናቆምና ሰላማዊ አቀራረብ ስናደርግ የኢህአሠ አባሎች ምን አይነት ትርጉም እንደሰጡት አላውቅም፡፡ በጠላትነት ዓይን እንዳማናያቸው ገብቷቸው ሊሆን ይችላል፤ ሳይጠነቀቁ ለማጥቃት ልናታልላቸው የሞከርን ሊመስላቸው ይችላል፤ ወይም ሰላም እንደምንፈልግ ቢገባቸውም ከታዘዙ ምንም ላያደርጉ ይችላሉ፡፡

ተሓህት/ህወሓት ከኢዴሕ ጋር አንድ አመት ተኩል የወሰደው ጦርነት ገብሩ እንደጠቀሰው በጥር አጋማሽ በድል ለማጠናቀቅ ብዙ የቀረው አልነበረም፡፡ ስለዚህ ተሓህት ከኢዴህ ጋር እየተዋጋ ስለነበረ ከኢህአሠ ጋር ለመዋጋት ሁኔታው እንደማይፈቅድለት የሚቀርበው ምክንያት ከእውነት የራቀ ነው፡፡

በዓጋመ ውስጥ በሁለቱ ድርጅቶች የነበረው ውጥረት እያየለ ይሄድ ነበር፡፡ በሠራዊቱ ለነበርነው መረጃ ሳይደርሰን የሆኑ የአካባቢው ሽማግሌዎች ተሰብስበው ህዝቡ ሁለት ድርጅቶች መሸከም ስለማይችል ኢህአሠ ከአካባቢው እንዲወጣ መጠየቃቸውንና በኢህአሠ መታሰራቸውን ’ስታስፈቷቸው እናያለን’ በሚል ዛቻ ከኢህአሠ አንድ ግለ ሰብ ሰማን፡፡ አስቀድሞ ባይነገረንም ሽማግሌዎቹ የወሰዱት እርምጃ በተሓህት ግፊት ብቻ ሊሆን እንደሚችል አያጠያይቅም፡፡

እርግጥ ህዝቡ ነፃነት ቢኖረውና ታጣቂዎችን ባይፈራ ማንንም የመቀለብ አቅም አልነበረውም፡፡ የሚሰጠን ሲያጣ በለስ (ቁልቋል) ብቻ ለቅሞ የሚሰጠን፣ በለሱን ምንም (እንደ ህዝቡ እንጀራ ወይም ጎመን) ሳይቀላቅልበት በመብላታችን ከኛ የተወሰኑ ታጋዮች በድርቀት እየታመሙ በህክምና እርዳታ የሚፀዳዱበት ሁኔታ ያጋጥመን ነበር፡፡ ሆኖም በነበረው ሁኔታ ህዝቡ በራሱ ተነሳሽነት እንኳንና በቦታው የቆየና በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ታጋዮች የነበሩትን ኢህአሠን ካካባቢው እንዲወጣ ሊጠይቅ፣ ጠንከር ያለ የሽፍቶች ቡድንም ቢያጋጥመው (ተሓህት በነበረበት አካባቢ ሽፍቶች መኖር አይችሉም ነበር) ኖሮ ካካባቢው ሊያስወጣ አይችልም ነበር፡፡

የተወሰኑ ሰዎች ኢአሠን ለመቃወም በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ እምበይቶ በሚባል ጎጥ ኗሪ የነበሩት አቶ ግርማይ የዕብዮ የሚባሉ የተሓህት የሚሊሽያ አባል የሁለቱም ድርጅቶች አባሎች ልጆቻችን ቢሆኖም ’ከወንድማማቾችም መንትዮች ይቀራረባሉ’ ብሎው ምሳሌ በመስጠት ኢህአሠ ካካባቢው እንዲወጣ ተናገሩ፤ በ25 የካቲት 1970 የኢህአሠ ሰዎች ሰውየውን ተከታትለው ገደሏቸው፡፡

በ26[13] የካቲት ወደ 11 ሰዓት ገደማ ተኸለ ሽሪፎ የሚባል የሃይላችን ሃኪም እየሮጠ መጥቶ ዓይጋ

---

12 ቀኑም እኔ እንደማስታውሰው በ27 እንጂ በ20 የካቲት አልነበረም፡፡ ካሓሳይ አብርሃ በመጋቢት 5 በማይ መሬት/ነበለት የተደረገውን ወግያ ሲጠቅስ የሶበያው ከ9 ቀኖች በፊት እንደነበረ ስለጠቀስ እኔ በ27 የካቲት ከምለው ጋር ይስማማል፡፡ ገፅ 373 የአሲምባ ፍቅር 2ኛ እትም፣ 2005

የነበረው የተሓህት የህክምና ቦታ በኢህአሠ እንደተጠቃ፣ በህክምና ላይ የነበሩ አባሎች ሊያመልጡ እንዳልቻሉ፣ እሱ ግን አምልጦ እንደመጣ ነገረኝ፡፡ ስብሓት ከኛ ትንሽ ራቅ ብሎ ከኢህአፓ አመራር ጋር ይወያይ ስለነበረ ዓይጋ ላይ የተፈፀመውን ጥቃት እንዲነገረው አደርከሁ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ስብሓት ከሱ ጋር ለነበሩ የኢህአፓ አመራር አባላት የሰማውን እንደነገራቸውና ለጉዳዩ ክብደት እንዳልሰጡት ነገረኝ፡፡
ገብሩ አንደገለፀው፣ ኢህአሠ የተሓህት የዓይጋ የህክምና ቦታን ማጥቃቱ ባንድ በኩል ሁለቱም ሲፈፅሚቸው ከቆዩት የግለ ሰቦች ስሜታዊና ድንገተኛ የመገዳደል ድርጊቶች አልፎ በእቅድ ወስኖ ወደ ውግያ መሸጋገሩን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የኢህአፓ አባል የነበረው (አሁን ዴንማርክ ያለው) በየነ ገብራይ እንደነገረኝ በሚቀጥለው ቀን ውግያ እንዳይቀጥል ለማድርግ በኢህአፓ አመራር ለሚመለከታቸው የሚያደርሰው ደብዳቤ ተሰጥቶት ነበር፡፡ ስለዚህ በኢህአፓ ውስጥ ከተሓህት ጋር መዋጋት የሚፈልጉና የማይፈልጉ ቡድኖች የነበሩ ይመስላል፡፡

በትግራይ ውስጥ የሽምጥ ተዋጊዎች እርስ በርሳቸው ሲዋጉ አንዱ ሌላውን እስኪያሸንፍ ፋታ አይሰጣጡም ነበር፡፡ ከደርግ ጋር መዋጋት ግን ፋታ የሚነሳ አልነበረም፡፡ ደርግ አልፎ አልፎ ዘመቻዎች እስኪያካሂድ ድረስ ሽምጥ ተዋጊዎቹ  በመረጡት ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ መዋጋትም አለመዋጋትም ይችሉ ነበር፡፡ ስለዚህ ተሓህት የውግያ ልምድ ነበረው፤ ኢዴህን አሸንፎ ስለነበረም የደርግ ዘመቻ ባልነበረበት ጊዜ ከኢህአሠ ጋር ለመዋጋት የሚስማማው ሁኔታ ነበር፡፡

በተሓህት በኩል የሽማግሌዎቹ ትንኮሳ እንደሚያመለከተው ባለው ዝግጁ ሠራዊት ላይ የስነ ልቦና ቅስቀሳና ኢህአሠን ከህዝብ ጋር የማጋጨት ስልት እየተካሄደ ግልፅ የማጥቃት እርምጃ ባልተወሰደበት ጊዜ ኢህአሠ ራሱ ዓይጋ ላይ ማጥቃት ስለጀመረ ወጥመድ ውስጥ ገባ፡፡

ገብሩም አኪሊሉን በሚመለከት እንደጠቀሰው፣ ስብሓት አኪሊሉ የሚባል ወጣት ተሓህትን የከዳ መስሎ ኢህአሠን ተቀላቅሎ እየሰለለ ከቆየ በሁዋላ መመለሱን እና ኢህአፓ ከተሓህት ጋር ያለውን ቅራኔ በብረት ሃይል ሊፈታው መወሰኑን መስማቱን ነግሮኝ ነበር፡፡ እኔም መረጃው እውነት ይሁን አይሁን አስፈላጊ ጥንቃቄዎች ማድረግ ጀመርሁ፡፡ አንድ ጊዜ ስብሓት፣ ኢህአሠዎች እንቅስቃሴያቸውን እያሰፉ ዓሲንባንና ፀለምቲን በሓሓይለ (በአድዋ ውስጥ የሚገኝ ቦታ) በኩል እያገናኙና እየተጠናከሩ እንደሆነ ሲነግረኝ የመረጃ ጉዳይ ሳይሆን ሳይበልጡን አንድ ነገር ማድረግ አለብን የሚል መንፈስ እንደነበረው ስለተሰማኝ መልስ አልሰጠሁትም፡፡ በሰላመዊ ውድድር ግን ተሓህት በህዘቡ ተቀባይነትእንዲያገኝ የቻልኩትን ሁሉ አደርግ ነበር፡፡

**የሶበያ ውግያ፡**

በዓይጋ ላይ በተፈፀመው ጥቃት ውግያው በኢህአሠ ስለተጀመረ እኛም ብንዋጋ ውግያ ላለመጀመር በሃይል ደረጃ ያደረግነውን ውሳኔ አያፈርስም ነበር፡፡ ሰላማዊ መፍትሂ  እንደማይገኝለት ግን እርግጠኞች አልነበርንም፡፡ ለማንኛውም ከ26 ወደ 27 የካቲት በሚያጠባው ሌሊት በጨለማ የሰነበትንባቸውን ቤቶች ትተን ሌሎች ለመከላከል የሚያመቹን የምናርድርባቸውን ቤቶች ያዝን፡፡ በ27 ጠዋት ልክ በ12 ሰዓት ተኩስ ተጀመረ፡፡

እኔ ወደተተኮሰበት ቦታ በሩጫ ስሄድ ኢህአሠዎች እየተንጫጩ ሲሮጡ አንዳንዶቹ፡ "ጓዶች እኛኮ ነን" ይሉ ስለነበር ለመዋጋት ሳያስቡ እንደተተኮሰባቸው ተሰማኝ፡፡ የሚተኩሱትን እንደያቆሙ ስነግራቸው የሃይሉ የሁለተኛው የመቶ አዛዥ ሃይለስላሴ (ሃለቃ) ስለሰማኝ አንድ ባንድ እየተቆጣጠረ ተኩሱን አስቆመው፡፡ ገና ሲተኩሱ ወደነበሩት ሳልደርስ ከግራዬ በኩል ከእነሱ 50 ሜትር ገደማ ሲቀረኝ በቀኜ በኩል ኢህአሠዎች 150 ሜትር ያህል ርቀው ከለላና መከላከያ ያለው ቦታ ያዙ፡፡ እንዳጋጣሚ በሁለቱም መካከል ነበርሁ፡፡

አጠገቤ ወደነበረው ገዢ መሬት (ከፍ ያለ ቦታ) ወጥቼ ሁኔታውን ለማረጋጋት ስሞክር ተወርውሬ ወደቅሁ፤ የሴኮንዶች ልዩነት ቢሆንም ከወድቅሁ በሁዋላ ተኩስ ሰማሁ፡፡ ጥይት አልነካኝም፡፡ እንደሚመስለኝ የወድቅሁት ጥይት በፈጠረው የአየር ክፍተት (vacuum) ምክንያት ነው፡፡) ከዛ

13 አስማማው በመፅሓፉ ገፅ 242 ዐይጋ ላይ የነበረው የተሓህት የህክምና ማእከል በኢህአሠ የተጠቃው ከሰቦያው ውግያ በሁዋላ እንደነበረ የገለፀውና ሃይል 74 የሶበያውን ግጭት አታውቅም ነበር ያለው ተሳስቷል፡፡ አስማማው ሃይሉ፤ ኢህአሠ /የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት/ ከ 1964 እስከ 1970 ዓ/ም ቅጽ አንድ፣ 2003 ዓ/ም

በሁዋላ ጨለማ እስኪለያየን ድረስ ተኩሱ አልቆመም፡፡

ከገለፅኩት ሁኔታ መረዳት እንደሚቻለው የተኮሱት የተሓህት አባላት ያደሩበት ብዙ ጊዜ ታጋዮች በሚያድሩበት ቤትና ወደ ቤቱ ለመተኮስ የሚመቹት ቦታዎችን እየጠበቁ ነበር፡፡ ደፈጣ አልነበረም፤ ምክንያቱም ማን፣ መቼ፣ በየት በኩል እንደሚመጣ አናውቅም ነበር፡፡ ኢ.ህአሠዎችም ተሰልፈው በመንገድ በመሄድ ላይ ስለነበሩ፣ ባይረ በኩል ሰበያ ሲደርሱ፣ በዛች ቦታና በዛ ሰዓት እዛ የነበረውን ሃይል ለማጥቃት የመጡ አይመስሉም፡፡ ከዓይጋ በሁዋላ በቀን ብርሃን ከሩቅም ሁለቱ ሰራዊቶች ቢተያዩ እንደማይዋጉ ዋስትና ባይኖርም ውግያ የተጀመረው ለሁለቱም በድንገት ነበር፡፡ኢ.ህአሠ መንገድ ይዞ ሲሄድ ተሓህት ወዳደረበት ቤት ተጠጋ፤ ተሓህት ማነህ ሲል ኢ.ህአሠ ገገር መሬት ለመያዝ ሞከረ፣ ገገር መሬቱ ተይዞ ስለነበረ ከዛ ተኩስ ተከፈተ፡፡

ቦታው ዓሲምባ፣ ማለትም የኢ.ህአሠ ሰፈር አጠገብ ስለነበረ ተሓህት እዛ የነበረው አንድ ሃይል ብቻ በመሆኑ ሃይሉን እስኪያሰባስብ ድረስ አንዱን ሃይል ወደ አድዋ እንዲያፈገፍግ አደረገ፡፡በውግያው ከሃይሉ ሁለት ቀላል የመቁሰል ጉዳት የደረሰባቸው ግን ውግያውን የቀጠሉ የተሓህት አበሎች ነበሩ፤ የተሰዋ አልነበረም፡፡ እኔ እንደሞትኩም እንደቆሰልኩም ተወርተዋል፤ ተፅፈዋል፤ ስለዚህ መውደቄን ያስተዋሉ መኖር አለባቸው፡፡ ከተሓህት በኩል ተኩስ ከቆመላቸው በሁዋላ ኢ.ህአሠዎች ተኩስ መጀመራቸውን በሚመለከት መመራመር የሚያስፈልግ አይመስለኝም፤ ምክንያቱም የሞትና የህይወት ጥያቄ የቅፅበት ጥያቄ በሚሆንበት ሁኔታ ሁሉም ታጣቂ ተረጋግቶ እንዲታገስ መጠበቅ ይከብዳል፡፡

ኢ.ህአፓ ጦርነቱን እንደፈለገው ሊታይ የቻለው ሃይሉን ወደ አድዋ አከታትሎ ካሰማራ በሁዋላ ነበር፡፡ ኢ.ህአሠ በ4 መጋቢት ፈረስማይ አካባቢ ሁለት እህል በመሸመት ላይ የነበሩ የሻዕብያ ታጋዮች (የተሓህት መስሎት) ትጥቃቸውን አስፈትቶ ካንገላታቸው በሁዋላ ለቀቃቸው፡፡ ሌሊት ማይ መሬት ላይ (ነበለት አጠገብ) የተሓህት ሃይል 73 እና የኢ.ህአሠ ሃይል 74 እየተዋጉ አድረው ሁለቱም በጣም ተጎዳድተው ሲነጋ የሃይሉ ኮሚሳር ስለተሰዋና የሃይሉ ምክትል አዛዥ ስለቆሰለ ሓየሎም ብቻው ሃይሉን እያስተባበረ በመገናኛ ረድዮ ሃይል 30ን ለእርዳታ ጠራ፡፡ ሃይል 74 ጠንክሮ ቢዋጋም ከተዳከመ በሁዋላ ስለተከበበ በ5 መጋቢት መቋቋም ስላልቻለ ያላመለጡና በህይወት የተረፉ ተማረኩበት (የተማረኩት ከዘጠኝ ቀኖች በፊት ሶበያ ላይ ስንዋጋ በዓጋመና ዓድዋ መካከል ገገር መሬት ይዘው እንደነበሩ ነግረውናል)፡፡

ከሁለት ሳምንት በሁዋላ እንደገና በዛ ያለ የኢ.ህአሠ ሠራዊት የተሓህት ሃይሎች 30 እና 73 ወደነበሩበት ስለመጣ በ19 መጋቢት በብዘትና አካባቢዋ አሰቃቂ ውግያ ተደረገ፡፡ ኢ.ህአሠዎች በጥንቃቄ የሚወጣ ገደል እየወጡ ከተሓህት ሃይል ጋር ሲዋጉ በጀርባቸው በኩል ሌላ ሃይል ስለገባ መውጣትም፣ መውረድም መቆምም ስላልቻሉ የጥይት ዒላማ የሆኑበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ከተሓህቱ ሃይል በስተጀርባ ራቅ ብሎ የኢ.ህአሠ ሃይል 500 ወደ ውግያው ከመግባቱ በፊት ሽሬ የነበሩ የተሓህት ሃይሎች ደርሰው ተኩስ ከፈቱ፡፡ መሸ፡፡ ሌሊትም መጠነኛ ውጊያ ነበር፡፡ ጠዋት ከተዋጉት የተረፉት ኢ.ህአሠዎች ተበታተኑ፡፡

ከሚያዝያ 27 ማለዳ ጀምረው እስከ ግንቦት 1 ድረስ የተሓህት ሃይሎች ኢ.ህአሠን በማጥቃት ከዓሲምባና ከአካባበው አስወጥተው እስከ ኤርትራ ሲከታተሉት ተሓኤ (ጀብሃ) ለኢ.ህአሠ ጥገኝነት እንደሰጠው ለተሓህት ካሳወቀ በሁዋላ ውጊያው መኸታ በሚባል ቦታ ላይ ቆመ፡፡

በማጠቃለል፣ ገብሩ በመፅሃፉ በተሓህት ውስጥ ከኢ.ህአፓ ጋር መዋጋት የሚፈልጉና የማይፈልጉ እንደነበሩ ቢጠቅስም ወደ ዝርዝር አልገባም፡፡ በዚያን ጊዜ በተሓህት ውስጥ አመራሩ በማድረግ ላይ በነበረው ምንጠራ አለመተማመን ሰፍኖ ስለነበረ የያንዳንዱ አቋም በዝርዝር ማወቅ አስቸጋሪ ነበር፡፡ እኔም አስተያየት መስጠት የምችለው የተወሰኑ ድርጊቶችን እና አጋጣሚዎችን በማስታወስ ነው፡፡ ስብሓት በግልፅ ኢ.ህአሠን እናጥቃ ሳይል ኢ.ህአሠ እየተጠናከረ በመሄድ ላይ እንደነበረና ተሓህትን ማጥቃቱ እንደማየቀር በመግለፅ ለውግያ የስነ ልቦና ዝግጅት እንዲኖር ያደርግ ነበር፡፡ ቀደም ብየ እንደጠቀስኩትም ሽማግሌዎቹ ኢ.ህአሠን ከአካባቢው ለማስወጣት መቅሰቀሳቸው ካለ ታጋዮች ግፊት ሊሆን አይችልም፤ ታጋዮቹም በቦታው የነበረው ስብሓት ሳያዛቸው ወይም ቢያንስ ሳያውቅ ሽማግሌዎቹን ለአደጋ የሚጋልጥና (ሽማግሌዎቹን በመግደልና በማሰር) ኢ.ህአሠን የሚያሳስት እርምጃ አይወስዱም ነበር፡፡

በአቋማቸው ፀንተው መቀጠላቸው ወይም አለመቀጠላቸው ባላውቅም ገብሩ፣ ስየና ፃድቃን ከኢ.ህአፓ

ጋር ግጭት አይፈልጉም ነበር፡፡ ገብሩ የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ከመሆኑ በፊት በ1969 በክረምት ጊዜ ዓዲ አርጉድ በሚባል መንደር መለስ ከኢህአፓ ጋር ቅራኔ እንደሚያባብሱብን ነግሮኝ ነበር፡፡ ብዘት ላይ አንድ ካሕሳይ ገብረዮሃንስ የሚባል ተሓህትን ከድቶ ኢህአሠን የተቀላቀለ ሚሊሽያ በ1969 ባንድ የተሓህት አባል ከተገደለ በሁዋላ ኢህአሠዎች እንትጮ ላይ አንድ የተሓህት ሚሊሽያ አቆሰሉ ሌላ አርሶ አደርም ገደሉ (እኛ በወቅቱ ያመንነው ካሕሳይ ገብረዮሃንስን ለመበቀል እንዳደረጉት ነበር)፡፡ ከዛ ብዘት ላይ 'የጓድ ካሕሳይ በሺ .....እንበቀላለን' እያሉ በቁጣ መፈክሮች ያስሰሙ ነበር፡፡

ሁለት ሃይሎች ባካባቢው ስለነበርን ወደ ብዘት መግባታችንና አለመግባታችን ከኢህአሠ ጋር ውግያ የመጀመርና ያለመጀመር ጥያቄ ሆነብን፡፡ ፃድቃን እና እኔ ለሰላማዊ መፍትሄ እድል ለመስጠት እንታገስ ስንል ሓየሎም እንግባ አለ፡፡ ስየም ጦርነት የሚያስጀምረን እርምጃ እንድንወስድ እንደማይፈልግ ገለፀ፤ ሓየሎምም ከሶስታችን ጋር ስለተስማማ ሳንዋጋ ቀረን፡፡
እንደ ገብሩ ተመሊሽ ሳየው፣ በተሓህት ውስጥ ሆነን ከኢህአፓ ጋር መሰረታዊ ቅራኔ እንዳልነበረንና መዋጋት እንዳልነበረብን ያመንነው በስልጣን ሽኩቻ ከመጠፋፋት ባህላችን አንፃር ሲታይ እምነታችን አለመስራቱ አይገርምም፡፡ አልተማርንበትም እንጂ በታሪካችን በእርአያነቱ ልዩ ቦታ ያለው የአፄ ዮሃንስና የንጉስ ምኒልክ (አፄ ከመሆናቸው በፊት) መቻቻል ነበር፡፡ እየቆየ ግልፅ እንደሆነውም ዓላማቸው ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል እንደሆነ ፅፈው የነበሩት ሰዎች ተሓህትንም ስለተቆጣጠሩ ተሓህት የነሱ ዓላማ ማስፈፀሚያ ነው፡፡ ስለዚህም በሉአላዊነት ጥያቄ የተሓህት ማኒፌስቶ ፀሓፊዎችና ኢህአፓ መሰረታዊ ቅራኔ ነበራቸው፡፡ በወቅቱ ውግያውን ለማቆም የሞከርኩት በሁለቱም ድርጅቶች የነበሩ ለለውጥ በህይወታቸው ለመክፈል የተዘጋጁ ወጣቶች እርስ በርሳቸው መተላለቅ እንደሌለባቸው በነበረኝ ፅኑ እምነት ምክንያት ነበር፡፡ የሁለቱ ድርጅቶች መዋጋት በዛን ጊዜ እንዳሳዘነኝ አሁንም መዋጋት እንዳልነበረባቸው አምናለሁ፡፡

በማጠቃለል ሲታይ የገብሩ መፅሓፍ ብዙ ሰዎች አንበውታል፤ እስካሁንም መፅሃፉን ለመግዛት ከተለያዩ አገሮች የሚጠይቁ አሉ፡፡ ገብሩ በመፅሃፉ ባነሳቸው ጉዳዮች የሚስማሙና የማይስማሙ አስተያየቶች መብዛታቸውም መፅሓፉ ውይይት እንዳቀጣጠለ ያመለክታሉ፡፡ አገዛዙን ከሚደግፉ ድረ-ገፆች ከመፅሃፉ አዎንታዊ ገፅታዎች ማየት መቻላቸው ጤነኛ ክስተት ነው፡፡ ገብሩ ከገለፃቸው ሂደቶችና አስተያየቶች የማይገናኙ፣ የሰውየውን ስብእና ለማጣጣል ሙያቸው ባልሆነ የስነ ልቦና ትችት የሚፅፉም አሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች የሚደገፉበት ምክንያት ሳይገልፁ መለስን ደግፈው ሲፅፉ ስለ ሉአላዊነትና ዴሞክራሲ አስተያየት ሳይሰጡ ይቀራሉ፡፡ በገብሩ መፅሃፍ ምክንያት በትግርኛ ከአረጋዊ በርሀ ጋር በጥር ወር ቃለ ምልልስ እንዳደረገው የአሜሪካ ድምፅ ረድዮ ጣብያ ባለደረባም በይዘት ላይ ማን ምን አይነት አቋም ለምን እንዳረመደ፣ ለህዝብና ላገር የትኛው በምን ምክንያት እንደሚጠቅም፣ ስለ ፍትሃዊነትና ዴሞክራሲያዊነት በመጠየቅ ፈንታ ቁም ነገሩን በዋናነት እንደ ግጥሚያ በማቅረብ 'ተበልጣችሁ ነው? ተሸንፋችሁ ነው? ሲል ውይይቱን የቦክስና የእግር ኩዋስ ዜና ያስመስለዋል፡፡

ገብሩ ያቀረባቸው ሃሳቦች የሉአላዊነት፣ የፍትህ፣ የዴሞክራሲ፣ የሰላም፣ የእድገት ወዘተ. ጉዳዮችን ይመለከታሉ፡፡ እነዚህም ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን ኤርትራውያንንም ከነ ቀጣይ ትውልዶቻቸው የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ህወሓት/ኢህዴግ ከነደጋፊዎቹ በቃላት ቢቃወምም በድርጊት ገብሩ የፃፈውን ያረጋግጣል፡፡ ሆኖም በህወሓት/ኢህዴግ ውስጥ ቅን ሰዎች ካሉና አቅም ካላቸው፣ ወንጀለኞቹንና ሙሰኞቹን ከስልጣን አስወግደው፣ ጉልበትና ውሸት ሳይጠቀሙ፣ በፈጠራ ወንጅለው ያሰሯቸውን ፈትተው ህዝቡ በነፃነት የሚፈልገውን እንዲመርጥ በማድረግ ታሪክ የመስራት እድል አላቸው፡፡